# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው የመጀመሪያ መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበትም ጊዜ በ50 እና 54 ዓ.ም. መካከል እንደ ሆነ ይገመታል። ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በየአገሩ እየዞረ ሲያስተምር ሳለ፥ተሰሎንቄ ከተማ በቆየበት ጥቂት ጊዜ ውስጥ ያሳመናቸው በቁጥራቸው መጠነኛ የሆኑ ደቀመዛሙርት ነበሩ። እነዚህም ምዕመናን ከእምነታቸው የተነሣ መከራና ስደት ይደርስባቸው ነበር። ስለዚህም መከራውንና ስደቱን ሳይሰቀቁ በእምነታቸው ጸንተው በመገኘታቸው፥ ሐዋርያው እግዚአብሔርን በማመስገን፥ከእምነታቸው ጽናት እንዳይናወጡ ያበረታታቸዋል። ፍቅሩንም በዚሁ መልእክቱ ይገልጥላቸዋል። መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት የክርስቶስን ዳግም ምፅአት በማስመልከት ሲሆን፥በዳግም ምፅአቱም ክርስቲያኖች ያላቸውን የታመነ ተስፋ ያረጋግጥላቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 ከጳውሎስ፥ከሲላስና ከጢሞቴዎስ የተ
ላከ። የእግዚአብሔር አብና የጌታ የኢየሱስ
ክርስቶስ ወገን ለሆኑት፥ በተሰሎንቄ ቤተ
ክርስቲያን ለሚገኙ ምዕመናን። የእግዚአብ
ሔር ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።
2 ለጸሎት በቀረብን ቁጥር ስለ እናንተ
በማሰብ፥ ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባ
ለን። 3 ስለ እናንተ በምንጸልይበት ጊዜ፥
በሥራ የተገለጸው እምነታችሁ፥የፍቅራችሁ
ፍሬ የሆነው ጥረታችሁና ስለ ጌታ መም
ጣት ያላችሁ ጽኑ ተስፋ፥ከፊታችን ድቅን
ብሎ ይታየናል።
4 ወንድሞች ሆይ፥ እግዚአብሔር እንደ
ወደዳችሁና እንደ መረጣችሁ እናውቃለን።
5 ምክንያቱም፥ወንጌልን በሰበክንላችሁ ጊዜ
በቃላት ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይ
ልና በሙሉ ልብ ነበር። በእናንተ መካከል
የኖርነው ምሳሌያዊ ሕይወት፥ለምንሰብከው
ወንጌል፥ምስክርና መግለጫ ነበር። 6 ምንም
እንኳ መከራና ኀዘን ቢደርስባችሁም፥
ቃሉን ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኝ ደስታ ተቀ
ብላችሁ፥ እኛንና ጌታ ኢየሱስን የምትመ
ስሉ ሆናችኋል።
7 ስለዚህ በመቄዶኒያና በአካይያ ለሚገኙ
ክርስቲያኖች ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸዋል።
8 በመቄዶኒያና በአካይያ ብቻ ሳይሆን፥በየቦ
ታው ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ
አማካይነት፥ ተሰራጭቷል። በየሄድንበት
ቦታ፥ሰዎች ሁሉ እኛ ስለ እናንተ መናገር
ከመጀመራችን በፊት አስቀድመው፥ በጌታ
ስላላችሁ ጽኑ እምነት ያወሩልናል። 9 ምን
ያህል እኛን በደስታ እንደ ተቀበላችሁና፥
እንዴትም ከጣዖት አምልኮ ተመልሳችሁ
ሕያዉንና እውነተኛውን አምላክ ማምለክ
እንደ ጀመራችሁ፥ የማይነግረን የለም።
10 እንዲሁም፥እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣ
ውንና፥ከሚመጣው አስቃቂ ፍርድ የሚያድ
ነንን የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግመኛ
መምጣት፥በናፍቆት የምትጠባበቁ መሆናች
ሁን ሰምተናል።

## ምዕራፍ 2

1 የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ
እናንተ መጥተን ያደረግነው ጉብኝት ምን

ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ራሳችሁ ታውቃላ
ችሁ። 2 ወደ እናንተ ከመምጣታችን፣በፊት
በፊልጵስዩስ ከተማ ምን ያህል መከራ እንደ
ደረሰብንም ታውቃላችሁ። ነገር ግን ከጠላ
ቶቻችን በዙ ተቃውሞ ቢያጋጥመንም፣የወ
ንጌሉን ቃል ለእናንተ መስበክ እንድንችል፣
እግዚአብሔር ድፍረትን ሰጠን። 3 ወንጌልን
የሰበክንላችሁ ፣ በስሕተት ወይም በርኩስ
ዓላማ ተመርቶን አይደለም። የነገርናችሁ
ሁሉ ከእውነተኛ ልብ የመነጨ እንጂ፣ማን
ኛችሁንም ለማታለል የታቀደ አልነበረም።
4 በዚህ ፈንታ ግን ቃሉን ስናውጅ፣ከእግ
ዚአብሔር አደራ እንደ ተቀበለ ታማኝ
መልእክተኛ ሆነን ነው። ሰዎችን ለማስደ
ሰት ብለን ፣ ከእውነተኛው የእግዚአብሔር
ቃል አንድም ነገር አንለውጥም። ምክንያ
ቱም ፣ የምናገለግለው ጌታ የልብን አሳብ
ሳይቀር ጠልቆ መመርመር የሚችል ነው።
5 ስለዚህ፣ራሳችሁ በሚገባ እንደምታውቁት
ሁሉ፣አንድ ጊዜ እንኳን ወንጌልን በሽንገላ
ቃል አለባብሰን፣ለእናንተ የሰበክንበት ጊዜ
የለም። ገንዘብ ስጡን ብለን እንዳልጐተጐ
ትናችሁም ፣ እግዚአብሔር ራሱ ምስክር
ነው። 6 ምንም እንኳ ሐዋርያት በመሆና
ችን የሚገባን ቢሆንም ከእናንተም ሆነ ከሌ
ሎች ምስጋናንና ክብርን አልፈለግንም።
7 እንደ ክርስቶስ ሐዋርያት ከእናንተ የሚገ
ባንን ለማግኘት መብት ነበረን። ነገር ግን፣
በመካከላችሁ የተመላለስነው ፣ ልጆቿን
በጥሩ እንክብካቤ እንደምታሳድግ እናት ፣
በአግባብና በርኅራኄ ነበር። 8 ከልብ ስለምን
ወዳችሁም፣የጌታን ቃል ብቻ ሳይሆን ሕይ
ወታችንንም እንኳን ለእናንተ አሳልፈን
ለመስጠት፣ደስተኞች ነበርን።
9 ወንድሞች ሆይ፣ለማንኛችሁም ሸክም
እንዳንሆን፣ቀንና ሌሊት ላባችንን በማንጠፍ
ጠፍ እየሠራን በመኖር ፣ የእግዚአብሔርን
ወንጌል እንደ ሰበክንላችሁ አታስታው
ሱም? 10 በእናንተ በአማኞች መካከል ያለ
ምንም ነቀፋ በትክክለኝነትና በንጽሕና
ለመኖራችን ፣ እግዚአብሔርም እናንተም
ምስክሮቻችን ናችሁ። 11 አባት ለልጆቹ እን
ደሚያደርገው ሁሉ፣እኛም ለእናንተ እንደ
ዚሁ አድርገንላችኋል። 12 የክብሩ ተካፋይ
እንድትሆኑ ወደ መንግሥቱ የጠራችሁን
አምላክ ፣ በኑሯችሁ ደስ እንድታሰኙት እየ
መከርን ብዙ አጽናንተናችኋል፤አበረታተና
ችኋልም።
13 የሰበክንላችሁን ወንጌል ፣ እንደ ሰው
ቃል ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል አድ
ርጋችሁ በመቀበላችሁ፣አምላካችንን አዘው
ትረን እናመሰግነዋለን። በእርግጥም የሰበክን
ላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ነበር። ይህም
ቃል በእናንተ በአማኞች ሕይወት ውስጥ
አሁንም ይሠራል።
14 ወንድሞች ሆይ፣በይሁዳ አገር የሚገ
ኙት የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያን
በሥጋ ከተወለዱቻቸው ከራሳቸው ወገኖች
ከአይሁድ መከራና ስደትን እንደ ተቀበሉ
ሁሉ ፣ እነሆ እናንተም ከራሳችሁ ወገኖች
መከራን ተቀብላችኋል። በዚህም በክርስቶስ
ኢየሱስ ያሉትን የይሁዳ ወንድሞቻችሁን
የምትመስሉ ሆናችኋል። 15 በይሁዳ ያሉ
ትን አብያተ ክርስቲያን የሚያሳድዱት እነ
ዚህ አይሁድ፣ከዚህ በፊት ነቢያትን ገድለ
ዋል፤ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስንም ሰቅለ
ዋል። አሁን ደግሞ እኛን ያሳድዱናል፤መከ
ራም ያሳዩናል። ይህንን በማድረጋቸው የሚ
ቃወሙት እኛን ብቻ ሳይሆን፣እግዚአብሔ
ርንም ጭምር ነው። 16 ይህንንም የሚያደር
ጉበት ዋናው ምክንያት፣አሕዛብ እንዲድኑ
ስለማይፈልጉ ነው። ስለዚህ እኛ እነርሱን
በመፍራት፣ለአሕዛብ ወንጌል መስበካችንን
እንድናቆም ይፈልጋሉ። በዚህም አድራጎታ
ቸው ኃጢአትን በኃጢአት ላይ እየጨመሩ
ይሄዳሉ። በመጨረሻም የእግዚአብሔር
ቁጣ መጥቶባቸዋል።
17 ወንድሞች ሆይ ፣ በመንፈስ ባንለያች
ሁም፣በሥጋ ከተለየናችሁ ቀን ጀምሮ እንደ
ገና መጥተን ልናያችሁ ጥረት አድርገን
ነበር። 18 እርግጥ፣እንደገና ዓይናችሁን ለማ
የት በጣም ጓጉተን ነበር። እኔ ራሴ ጳው
ሎስ፣ልመጣና ላያችሁ ብዙ ጊዜ ሞክሬአ
ለሁ። ነገር ግን፣ሰይጣን እንዳንመጣ አገ
ደን። 19 ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ በሚመጣ
በት ጊዜ፣ትምክህታችንና ተስፋችን፣እንዲ
ሁም የደስታችን ምክንያት፣ማን ይመስላች
ኋል? ጌታ ሲመጣ የድልን አክሊል እንድን
ቀበልና ደስታን እንድንቀዳጅ ፣ ምክንያት
የምትሆኑን እናንተ ናችሁ። 20 በእርግጥ ፣
እናንተ ትምክህታችንና ደስታችን ናችሁ።

## ምዕራፍ 3

1-3 በመጨረሻም መታገሥ ስላልቻልኩ
በአቴንስ ብቻዬን ቀይቼ፣ወንድማችንና በወ
ንጌል አገልግሎት የሥራ ባልደረባችን የሆነ
ውን ጢሞቴዎስን በእምነታችሁ እንዲያጸና
ችሁና እንዲያበረታታችሁ ፣ በደረሰባችሁ
መከራ ተስፋ እንዳትቆርጡ እንዲመክራ
ችሁ ፣ እርሱን ወደ እናንተ ለመላክ ወሰ

ንኩ። ይህንን ዓይነት መከራ እንድንቀበል፣
እግዚአብሔር የፈቀደው ነገር እንደሆነ
በሚገባ ታውቃላችሁ። 4 ከእናንተ ዘንድ
በሰነበትንበት ጊዜ፣ ይህን ዓይነት ስደትና
መከራ እንደሚያጋጥመን አስቀድመን ነግረ
ናችሁ ነበር። የነገርናችሁም አልቀረም፤እየ
ደረሰብን ነው።

5 ቀደም ሲል እንዳልኩት፣ መጥቼ ላያ
ችሁ የማልችል መሆኔን ሳውቅ ስለ እምነታ
ችሁ ማወቅ ፈልጌ፣ጢሞቴዎስን ወደ እና
ንተ ላክሁት። ይህንን ያደረግሁበት ምክን
ያት፣ ምናልባት ሰይጣን ፈትኗችሁ፣ እስከ
አሁን ድረስ በእናንተ መካከል ያደረግነው
ጥረት ሁሉ፣ ከንቱ እንዳይሆን በመሥጋት
ነው። 6 አሁን ግን ጢሞቴዎስ ወደ እኛ
ተመልሶ ከመጣ በኋላ፣ስለ ፍቅራችሁ ጽና
ትና ስለ እምነታችሁ ብርታት፣ደስ የሚያ
ሰኝ ወሬ አሰምቶናል። እንዲሁም ሁልጊዜ
በመልካም እንደምታስታውሱንና፣እኛ እን
ደምንመኘው ሁሉ፣እናንተም በዓይነ ሥጋ
ልታዩን የምትችሉበትን ጊዜ እንደምትና
ፍቁ ነግሮናል። 7 ይህንን በመስማታችን፣
እጅግ በጣም ተጽናንተናል። ስለዚህ ወንድ
ሞች ሆይ፣መከራና ችግር የደረሰብን ቢሆ
ንም፣እምነታችሁ ጽኑ መሆኑን በመስማታ
ችን እንድንበረታታ አድርጎናል። 8 የእናንተ
በእምነታችሁ ጸንታችሁ መቆም ለእኛ ሕይ
ወት ነው።

9 በእናንተ ምክንያት በእግዚአብሔር
በአምላካችን ፊት ስላለን ደስታ፣ እርሱን
የምናመሰግንበት ቃላት ያጥሩናል። 10 ስለ
እናንተም፣ ቀንና ሌሊት ባለማቋረጥ ወደ
እግዚአብሔር እንጸልያለን። የምንጸልየ
ውም፣ፊታችሁን ለማየት እንድንበቃና፣ከእ
ምነታችሁ የጐደለ ነገርም ቢኖር ያንን
ማሟላት እንድንችል ነው።

11 አባታችን የሆነው እግዚአብሔር፣እን
ዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓይነ
ሥጋ ልናያችሁ እንድንችል ያብቃን።
12 እኛ እናንተን እንደምናፈቅር ሁሉ እርስ
በእርስ መዋደድ እንድትችሉ፣ እግዚአብ
ሔር ፍቅሩን ይጨምርላችሁ። 13 ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ተመ
ልሶ በሚመጣበትም ጊዜ፣ ያለ ኃጢአትና
ያለ ነቀፋ በእግዚአብሔር ፊት መቆም እን
ድትችሉ፣እርሱ ልባችሁን ያጽና።

## ምዕራፍ 4

1-2 ወንድሞች ሆይ፣ አሁን እንደምትኖ
ሩት እግዚአብሔርን በሚያስደስት ሁኔታ
እንዴት መኖር እንደሚገባችሁ፣ከጌታ ኢየ
ሱስ በተቀበልነው ሥልጣን መሠረት ከዚህ
በፊት አስተምረናችኋል። አሁንም በጌታ
ስም የምናዛችሁና የምንለምናችሁ፣ በዚሁ
በተማራችሁት መሠረት፣በይበልጥ እግዚአ
ብሔርን በማስደሰት እንድትኖሩ ነው።
3-4 ከዝሙት ኃጢአት እንድትርቁና፣በቅድ
ስና በመኖር ቢጋብቻ ጸንታችሁ በንጽሕና
እንድትኖሩ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።
5 በጋብቻ ጸንታችሁ የምትኖሩበትም ምክን
ያት፣ እግዚአብሔርን የማያውቁት አሕዛብ
ከሚፈጽሙት ከፍትወት እንድትርቁ ነው።

6 በዚህ ነገር ማንም ወንድሙን አይበ
ድል። ከዚህ በፊት እንደ ነገርኋችሁ፣እንደ
እነዚህ ያሉትን ነገሮች የሚያደርገውን
ሰው፣እግዚአብሔር ይቀጣዋል። 7 እግዚአብ
ሔር የጠራን በቅድስናና በንጽሕና እንድን
ኖር እንጂ፣ በርኩሰት እንድንኖር አይደ
ለም። 8 ይህንንም የሚቃወም ሰው ካለ፣
እርሱ የሚቃወመው ከሰው የተሰጠውን
ትእዛዝ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስን የላከላች
ሁን እግዚአብሔርን ራሱን ነው።

9 በምዕመናን መካከል መኖር ስለሚገ
ባው የወንድማማች ፍቅር፣ በተጨማሪ
ማተት የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ምክን
ያቱም፣እርስ በእርስ እንድትፋቀሩ እግዚአ
ብሔር ራሱ እንዳስተማራችሁ፣ እርግጠኛ
ስለሆንኩ ነው። 10 በመቄዶንያ ላሉት ክርስ
ቲያን ወንድሞቻችሁ ምን ዓይነት ፍቅር
እንዳላችሁ እናውቃለን። የምንለምናችሁ
ነገር ቢኖር ይህንኑ እንድትቀጥሉበት ነው።
11 በጸጥታና በእርጋታ ኑሩ። የራሳችሁን
ሥራ እንደሚገባ የምትፈጽሙበትን መን
ገድ ብቻ አስቡ። ከዚህ በፊት እንደነገርና
ችሁ፣በገዛ እጃችሁ እየሠራችሁ ለኑሮ የሚ
ያስፈልጋችሁን ለማግኘት ተጣጣሩ። 12 ይህ
ንን ብታደርጉ፣የማንም ሰው ጥገኛ ሳትሆኑ
ለመኖር ትችላላችሁ። በጌታ ባላመኑ ሰዎች
ዘንድም የተከበራችሁ ትሆናላችሁ።

13 ወንድሞች ሆይ፣ተስፋ እንደሌላቸው
ሰዎች እንድታዝኑ ስለማንፈልግ፣በሞት ስለ
ሚለዩዋችሁ ክርስቲያኖች፣ አንዳንድ ነገሮ
ችን እንድታውቁ እፈልጋለሁ። 14 ክርስቶስ
እንደሞተና ከሞትም እንደተነሣ ካመንን፣
እንዲሁም ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ፣እግዚአብሔር
የሞቱትን ክርስቲያኖች ሁሉ ከእርሱ ጋር
ያመጣቸዋል።

15 ይህ የምነግራችሁ የጌታ የራሱ ቃል
ነው። ጌታ እስኪመጣ ድረስ እኛ በሕይ

ወት የምንቆየው፥በጌታ አምነው የሞቱትን
አንቀድማቸውም። 16 ጌታ ራሱ ፥ በታላቅ
የትእዛዝ ድምፅ፥በመላእክት አለቃ ድምፅና
በእግዚአብሔር መለከት የጥሪ ድምፅ ከሰ
ማይ ይወርዳል። በክርስቶስ አምነው የሞ
ቱት ክርስቲያኖች አስቀድመው ከሞት ይነ
ሣሉ። 17 ከዚያም እኛ በሕይወት ያለነው
ጌታን በአየር ላይ ለመገናኘት ፥ ከእነርሱ
ጋር በአንድነት በደመና እንነጠቃለን። ከጌ
ታም ጋር ለዘላለም እንኖራለን። 18 ስለዚህ
እርስ በእርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።

## ምዕራፍ 5

1 ወንድሞች ሆይ፥ታዲያ ይህ ሁሉ የሚ
ሆነው መቼ ነው? እርግጥ፥ይህ ሁሉ ስለሚ
ፈጸምበት ጊዜ ፥ ብዙ መናገር አያስፈልገ
ኝም። 2 ምክንያቱም ያ ቀን መቼ እንደሚ
ሆን ፥ ማንም እንደማያውቅ ተረድታችሁ
ታል። ሌባ ባልታሰበ ሰዓት በሌሊት እንደ
ሚመጣ ሁሉ ፥ እንደዚሁም ጌታ ባልታወ
ቀና ባልታሰበ ጊዜ ይመጣል። 3 ሰዎች ፥
«አሁን ሁሉ ነገር ሰላም ነው» ሲሉ በድን
ገት ጥፋት ይመጣባቸዋል። ሊያመልጡም
አይችሉም። ሴት ለመውለድ ምጥ እንደሚ
ያስጨንቃትም ይጨነቃሉ።
4 ወንድሞች ሆይ፥እናንተ ግን በጨለማ
ውስጥ ስላይደላችሁ፥የጌታ ቀን እንደ ሌባ
በድንገት አይመጣባችሁም። 5 እናንተ የብር
ሃን ልጆችና በብርሃን ውስጥ የምትመላለሱ
ሰዎች ናችሁ እንጂ፥የጨለማ ልጆች አይደ
ላችሁም። 6 ስለዚህ ፥ እንደ ሌሎቹ ሰዎች
እንዳታንቀላፉ ተጠንቀቁ። የጌታንም
መምጫ ቀን፥ተግታችሁ ጠብቁ። 7 ሌሊት፥
ሰዎች የሚያንቀላፉበትና የሚሰክሩበት ጊዜ
ነው። 8 ነገር ግን እኛ በብርሃን የምንመላ
ለስ ሰዎች ስለሆንን ራሳችንን በመግዛት
በመጠን እንኑር። እምነትንና ፍቅርንም
ተጐናጽፈን፥ደኅንነትን እንደ ራስ ቁር እና
ጥልቅ።
9 እግዚአብሔር የመረጠን ቁጣው እንዲ
ወርድብን ሳይሆን፥በጌታ በኢየሱስ ደኅንነ
ትን እንድንቀበል ነው። 10 ብንሞትም ሆነ
በሕይወት ብንኖር ፥ ከእርሱ ጋር ለዘላለም
እንድንኖር ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶልናል።
11 ስለዚህ አሁን እንደምታደርጉት ፥ ወደፊ
ትም አንዱ ሌላውን ያበረታታው።
12 ከክፉ እንድትጠበቁ የሚመክሯች
ሁን ፥ በትጋት የሚያገለግሏችሁንና በጌታ
የሚያስተዳድሯችሁን የቤተ ክርስቲያን
መሪዎች ፥ አክብሩ። 13 በትጋት የሚያገለግ
ሉና የሚደክሙ ስለሆነ፥ታላቅ አክብሮትና
ፍቅር አሳዩአቸው። እርስ በእርሳችሁ አት
ጣሉ።
14 ወንድሞች ሆይ ፥ ሰነፎችን ምከሩአ
ቸው፤የሚፈሩትንም አደፋፍሯቸው፤ደካማ
የሆኑትን አበረታቷቸው፤ሰውን ሁሉ በትዕግ
ሥት ተቀበሉ። 15 ለማንም ክፉን በክፉ
አትመልሱ። ነገር ግን እርስ በእርሳችሁም
ሆነ ለሌሎች ሰዎች፥ሁልጊዜ መልካም ነገ
ርን አድርጉ። 16 ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ።
17-18 ሳታቋርጡ ጸልዩ። በክፉም በደጉም
ለእግዚአብሔር ዘወትር ምስጋና ስጡ።
ይህን በክርስቶስ ጸንታችሁ እስካላችሁ
ድረስ፥እግዚአብሔር ራሱ እንድትፈጽሙት
ያቀደውና የሚፈልገው ሥራ ነው።
19 የመንፈስ ቅዱስን እሳት አታጥፉ።
20 ትንቢትን አትናቁ። 21 ሁሉን ነገር መር
ምሩ መልካም የሆነውን ብቻ ያዙ። 22 ከማ
ንኛውም ክፉ ነገር ራቁ። 23 ጌታ ኢየሱስ
ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ በፊቱ ያለነቀ
ፌታ እንድትገኙ፥የሰላም አምላክ እግዚአብ
ሔር መንፈሳችሁን ፥ ነፍሳችሁንና ሥጋች
ሁን ፈጽሞ ይቀድስ። 24 ልጆቹ እንድት
ሆኑ የጠራችሁ እግዚአብሔር ፥ በገባላችሁ
ተስፋ መሠረት ፥ ይህንን ሁሉ ይፈጽምላች
ኋል።
25 ወንድሞች ሆይ ፥ ለእኛ ደግሞ ጸልዩ
ልን። 26 ከእናንተ ጋር ላሉት ወንድሞች
ሁሉ ፥ በፍቅር መሳሳም ሰላምታችንን አቅር
ቡልን። 27 ይህንን የጻፍኩትን ደብዳቤ ለክ
ርስቲያኖች ሁሉ እንድታነቡላቸው ፥ በጌታ
ፊት አደራ እላችኋለሁ።
28 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ከሁ
ላችሁ ጋር ይሁን።

የናንተው
ጳውሎስ

## ሐዋርያው ጳውሎስ

# ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው ሁለተኛው መልእክት

### መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፥የተጻፈበት ዘመን ደግሞ፥በ50 እና በ54 ዓ.ም. መካከል ባለው ጊዜ እንደሆነ ይገመታል። የመልእክቱ መሠረተ ሐሳብ የክርስቶስን ዳግም ምፅአት የሚመለከት ነው። ይህን በሚመለከት አንዳንድ ሐሰተኞች መምህራን ተነሥተው የተሰሎንቄን ምዕመናን በትምህርታቸው በክለው አስጨንቀዋቸዋል፥ግራም አጋብተዋቸዋል። 'የጌታ ቁጣ የሚገለጥበት ያ የዓለም ፍጻሜ ይኸው መጥቷል። ለዚህ ሁሉ መከራ፥ ለዚህ ሁሉ ስደት ምክንያቱስ ይህ ሳይሆን ይቀራል?' ብለው አስተምረዋል። ጳውሎስም በዚህ መልእክቱ የጌታ ቁጣ የሚገለጥበት የፍርድ ቀን ገና ያልመጣ መሆኑን ይገልጽላቸዋል። ያ ቀን ከመድረሱም በፊት አንዳንድ ነገሮች መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አስረድቶ ያረጋጋቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 የአባታችን የእግዚአብሔር፥የጌታችንም
የኢየሱስ ክርስቶስ ወገን ለሆኑትና በተሰሎ
ንቄ ለሚገኙት ምዕመናን፥ከጳውሎስ ከሲላ
ስና ከጢሞቴዎስ የተላከ።
2 የእግዚአብሔር አብ፥ የጌታ የኢየሱስ
ክርስቶስም ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።
3 ወንድሞች ሆይ፥ መደረግ የሚገባውና
ተገቢ ነገር መሆኑን በማመን፥ስለ እናንተ
እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። እግዚአብ
ሔርን የምናመሰግንበትም ምክንያት፥በእም
ነት እያደጋችሁና፥እርስ በእርስም ያላችሁ
ፍቅር እየጨመረ በመሄዱ ነው። 4 ስደትና
መከራ ቢበዛባችሁም፥ በእምነት ጸንታችሁ
ቆማችኋል። ስለዚህ፥ ስለ እናንተ ለአብያተ
ክርስቲያን ሁሉ መናገር ደስ ይለናል።
5 ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅን መሆ
ኑን የሚያሳየን ማረጋገጫ ነው። ከዚህም
የተነሣ አሁን መከራ ለምትቀበሉለት ለመን
ግሥቱ እግዚአብሔር ብቁዎች አድርጎ ይቆ
ጥራችኋል። 6 መከራ ለሚያሳዩአችሁ መልሶ
መከራን ሲከፍል፥መከራ ለምንቀበል ለእናን
ተም ሆነ ለእኛ ዕረፍት ይሰጠናል።
7 ይህም የሚፈጸመው ጌታ ኢየሱስ በኃ
ያላን መላእክቱ ታጅቦ በሚንቀለቀል እሳት
ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ነው። 8 እግዚአ
ብሔርን በማይፈልጉትና፥የጌታችንን የኢየ
ሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማይታዘዙት ላይ
ይፈርድባቸዋል። 9 ከጌታና ከኃይሉም
ክብር ተለይተው፥ በዘላለማዊ ጥፋት ይቀ
ጣሉ። 10 ይህም የሚሆነው በቅዱሳን
ሕዝቡ ዘንድ ሊከበርና ባመኑትም መካከል
ሊወደስ ሲመጣ ነው። እናንተም እርሱን
ከሚያመሰግኑት መካከል ትሆናላችሁ።
ምክንያቱም፥ስለ እርሱ የነገርናችሁን ሁሉ
ሰምታችሁ አምናችሁበታልና።
11 ስለዚህ ለተጠራችሁበት ጥሪ፥እግዚአ
ብሔር ራሱ ብቁ እንዲያደርጋችሁ፥ መል
ካም ለማድረግ ያላችሁን ምኞትና በእም
ነት የምትሠሩትን ሥራ ከግቡ ለማድረስ፥
በኃይሉ እንዲረዳችሁ እንጸልይላችኋለን።
12 ይህን የምንጸልየውም የጌታችን የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ስም፥በእናንተ ምክንያት እን
ዲከበርና እናንተም በእርሱ እንድትከብሩ
ነው። ይህን ሁሉ እንድትፈጽሙ የሚያበቃ
ችሁ፥የአምላካችንና የጌታችን የኢየሱስ ክር
ስቶስ ረድኤት ነው።

## ምዕራፍ 2

1-2 ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ
መምጣትና፥ እኛም እርሱን ለመቀበል ስለ
ምንሰበሰብበት ሁኔታ፥የሚከተለውን አሳስባ
ችኋለሁ። አንዳንድ ሰዎች፥ጊዜው ደርሷል
በማለት በሚያወሩት ወሬ አትታወኩ፤ ሥጋ
ትም አይግባችሁ። 'የጌታ ቀን የደረሰ መሆ
ኑን የሚያረጋግጥ ትንቢት ደርሶናል'፥
ወይም ደግሞ፥ 'ከሐዋርያው ከጳውሎስ
ደብዳቤ ተጽፎልናል' የሚሉ ሰዎች ቢያጋ
ጥሙአችሁ፥ አትመኗቸው። 3 ማንም ሰው
በምንም መንገድ አያታልላችሁ። ያ ቀን
ከመድረሱ አስቀድሞ፥የመጨረሻው ዓመፅ

ይሆናል። ለጥፋት የተወሰነውም የዓመፅ
ሰው ይገለጣል። 4 ይህም የዓመፅ ሰው፣
ሰዎች አምላክ አድርገው ከሚያመልኩት
ነገር ሁሉ በላይ፣ ራሱን ከፍ ከፍ ያደር
ጋል። አምልኮንም ሁሉ ይቃወማል። እንዲ
ሁም፣ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ» እያለ፣ወደ
እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ገብቶ ይቀመ
ጣል። 5 ከእናንተ ጋር በነበርኩበት ጊዜ እን
ኳን፣ስለዚህ ጉዳይ እንደ ነገርኳችሁ ታስታ
ውሳላችሁ። 6 አሁን እንዳይገለጥ የሚያግ
ደው ነገር መኖሩም፣ ከእናንተ የተሰወረ
አይደለም። መገለጥ የሚችለውም ጊዜው
ሲደርስ ብቻ ነው።

7 ይሁን እንጂ፣ የዓመፅ ሥራ አሁንም
ቢሆን በስውር እየተፈጸመ ነው። ይህ የአ
መፁ ሰው፣ እስከ አሁን ድረስ እንዳይገለጥ
አግዶት ያለው ኃይል እስካለቀቀው ድረስ
ግን፣ ይፋ አይወጣም። 8 ይፋ እንዳይወጣ
ያገደው ኃይል ሲነሣ ግን፣ የአመፁ ሰው
ይገለጣል። ነገር ግን፣ ጌታ ኢየሱስ በሚገለ
ጥበት ጊዜ በእስትንፋሱ ያቃጥለዋል፤ በግር
ማውም ያጠፋዋል። 9 ይህም የኃጢአትና
የክፋት ሰው፣ የሰይጣን መሣሪያ ሆኖ ይመ
ጣል። በሰይጣን ኃይልም ተሞልቶ፣የሐሰት
ተአምራትን ምልክቶችንና ድንቆችን በመ
ሥራት ብዙዎችን ያታልላል። 10 የሚጠፉ
ትንም ለማሳሳት፣ ልዩ ልዩ የክፋት ድርጊቶ
ችን ይፈጽማል። እነዚህ ሰዎች የሚጠፉበ
ትም ምክንያት እውነትን ተቀብለው ማመ
ንና መዳን ሲቻላቸው፣ በእምቢተኝነት አሻ
ፈረኝ በማለታቸው ነው። 11 ከዚህም የተ
ነሣ፣ እግዚአብሔር ራሱ ሐሰትን እንዲቀበ
ሉና እንዲያምኑ ለኃይለኛ መታለል ይተዋ
ቸዋል። 12 ይህም የሆነበት ምክንያት፣ እው
ነትን የሚቃወሙ፤ ሐሰትን የሚቀበሉና
ኃጢአት መሥራትንም የሚወዱ ሁሉ፣ ይፈ
ረድባቸው ዘንድ ነው።

13 በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፣
ስለ እናንተ ግን፣ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን
ማመስገን አለብን። ምክንያቱም፣ እግዚአብ
ሔር እናንተን ከመጀመሪያው አንሥቶ በመ
ንፈስ ቅዱስ ተቀድሳችሁና እውነትንም
አምናችሁ እንድትድኑ መርጧችኋል።
14 የመረጣችሁም፣ በእኛ በተሰበከላችሁ የም
ሥራች ቃል አማካይነት ነው። ይህንንም
ያደረገው፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን
ክብር ተካፋይ እንድትሆኑ ነው።

15 ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣ አብረን ሳለን
ከሰበክንላችሁና፣ በመልእክቶቻችንም ካስተ
ማርናችሁ እውነት፣ ፈቀቅ አትበሉ።

16 ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዲ
ሁም ከፍቅሩ የተነሣ በጸጋው የዘላለምን
መጽናናትንና መልካም ተስፋን የሰጠን እግ
ዚአብሔር አባታችን፣ 17 ልባችሁን ያጽና
ኑት። መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ለመና
ገርና ለማድረግም፣ ብርታቱን ይስጧችሁ።

## ምዕራፍ 3

1 ወንድሞች ሆይ፣ ለእኛ እንድትጸልዩ
ላሳስባችሁ እወዳለሁ። የጌታ ቃል በየሥፍ
ራው በፍጥነት እንዲሠራጭና፣ በእናንተ
ሕይወት ውስጥ እንደታየው የሚሰሙትን
ሰዎች ሕይወት እንዲለውጥ፣ ጸልዩ። 2 እንዲ
ሁም፣ ከክፉ ሰዎች ወጥመድ እግዚአብሔር
እንዲጠብቀን ጸልዩልን። ምክንያቱም፣
ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ይወዱታል
ማለት አይቻልምና። 3 ጌታ ታማኝ ነው፤ እን
ድትጸኑ ያደርጋችኋል። ከሰይጣንም ጥቃት
ይጠብቃችኋል። 4 ያስተማርናችሁን ነገር
ሁሉ በሥራ ላይ እንድታውሉት፣ ጌታ ራሱ
እንደሚያስችላችሁ እርግጠኞች ነን። 5 ጌታ
ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር ፍቅርና ወደ
ክርስቶስ ትዕግሥት እንዲመራው እንጸልይ
ላችኋለን።

6 ወንድሞች ሆይ፣ የሚከተለውን ትእዛዝ
በጌታ ስም እንሰጣችኋለን። ለኑሮ የሚያስፈ
ልገውን ነገር፣ በእጁ ሠርቶ ማግኘት ከማይ
ወድ ሰነፍና ባስተማርናችሁ ትምህርት
መሠረት ከማይኖር ክርስቲያን ወንድም ጋር
ሕብረት አይኑራችሁ። 7 የእኛን ምሳሌ መከ
ተሉ ይጠቅማችኋል። ለመሆኑ፣ ያለ ሥራ
ቁጭ ብለን አይታችሁን ታውቃላችሁ?
8 በገንዘብ ካልሆነ በቀር፣ የሚያስፈልገንን
ነገር በነፃ ከማንም ሰው የተቀበልንበት ጊዜ
የለም። ለማንኛችሁም ሸክም እንዳንሆን
በማለት፣ ቀንና ሌሊት ተግተን እንሠራ
ነበረ። 9 የሚያስፈልገንን ነገር ከእናንተ
የመቀበል መብት፣ ሳይኖረን ቀርቶ አይደ
ለም። ነገር ግን ለኑሮ የሚያስፈልገውን
ለማግኘት፣ መሥራት እንደሚገባ ልናሳያ
ችሁ በማሰብ ነበር። 10 ከእናንተ ጋር በነበር
ንበት ጊዜ እንኳን፣ «የማይሠራ አይብላ»
የሚል ሕግ ሰጥተናችሁ እንደ ነበር ታስታ
ውሳላችሁ።

11 ከመካከላችሁ አንዳንዶች ሥራ ፈት
ተው፣ በሐሜትና በወሬ ጊዜያቸውን እንደ
ሚያባክኑ ሰምተናል። 12 እንደዚህ ያሉት
ሰዎች ይህንን ተግባራቸውን ትተው፣ ሠር
ተው እንዲኖሩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም እናዛቸዋለን። 13 እናንተም ወንድሞች

ሆይ ፣ መልካም ነገር ከማድረግ እንዳትቦ
ዝኑ፣አደራ እላችኋለሁ።
[14] በዚህ መልእክት ያዘዝናችሁን ቃል
መፈጸም የማይፈልግ ሰው ቢኖር ፣ እንዲህ
ያለው ሰው ማን እንደሆነ ካረጋገጣችሁ
በኋላ ፣ በሥራው እንዲያፍር ከእርሱ ራቁ።
[15] ሆኖም፣እንደ ጠላት አትቁጠሩት። እንደ
ወንድማችሁ በመመልከት፣ከስሕተቱ እንዲ
ታረም በምክር እርዱት።
[16] የሰላም ጌታ ራሱ ሁልጊዜ ፣ በሁሉ
ነገር ፣ሰላሙን ያብዛላችሁ። ጌታ ከሁላችሁ
ጋር ይሁን። [17] በደብዳቤዎቼ መጨረሻ ላይ
አዘውትሬ እንደማደርገው ሁሉ ፣ይህንን ሰላ
ምታ የጻፍኩላችሁ ፣ እኔው ጳውሎስ በገዛ
እጄ ነው። [18] የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
በረከት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

የናንተው
ጳውሎስ

# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለጢሞቴዎስ የጻፈው የመጀመሪያው መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ፣ነው። መልእክቱ የተጻፈበትም ጊዜ በ63 ዓ.ም. እንደ ሆነ ይገመታል። ወጣቱ ጢሞቴዎስ ፣ከሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት የተነሣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን በቅቷል። ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚመለከተው ልክ እንደ ልጁ አድርጎ ነበር። ጢሞቴዎስ በጌታ ካመነ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል ለምዕመናን ይሰብክና ያስተምር ነበር። ይህን የማስተማር ተግባሩን እንዴት ማከናወን እንዳለበትና እንደ ክርስቶስ አገልጋይ ምን ማድረግ፣እንዴትስ መኖር እንደሚገባው ለማስገንዘብ፣ሐዋርያው ይህን መልእክት ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል።

---

## ምዕራፍ 1

[1] በአዳኛችን በእግዚአብሔር አብ፣ተስፋ
ችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ
ሐዋርያ እንዲሆን ከተጠራው ከጳውሎስ ፣
[2] ለጢሞቴዎስ የተላከ።
በጌታ እውነተኛ ልጄ የሆንከው ጢሞቴ
ዎስ ሆይ ፣ የአባታችን የእግዚአብሔር የጌታ
ችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፣ ምሕረትና
ሰላም እንዲበዛልህ እመኝልሃለሁ።
[3-4] ወደ ሜቄዶንያ ለመሄድ ስነሣ እንደ
ነገርኩህ ፣ ከኤፌሶን ሳትወጣ የሐሰት ትምህ
ርት የሚያስተምሩትን ሰዎች መቋቋም አለ
ብህ። እነዚህ ሰዎች ተረት በመተረትና
ቧልት በማውራት የሚያዛምቱት የተሳሳተ
ትምህርታቸው እንዲገታ አድርግ። እንዲህ
ያለው ሁኔታ ሰዎች የእግዚአብሔርን ማዳን
በእምነት እንዲቀበሉ የሚረዳ ሳይሆን፣ጭቅ
ጭቅንና ክርክርን የሚፈጥር መጥፎ አዝማ
ሚያ ነው። [5] እኔ በበኩሌ የምናፍቀውና
የምጓጓው ፣ የክርስቲያኖች ሕይወት ከንጹሕ
ልብ ፣ ከበጎ ሕሊናና ቅንነት ከተሞላ እም
ነት በሚመነጭ ፍቅር ፣ ተሞልቶ ማየትን
ነው።
[6] እነዚህ የሐሰት መምህራን ከዚህ ከትክ
ክለኛው ነገር ስተው ሞኝነት በሞላበት
ክርክርና ጭቅጭቅ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ።
[7] እንደ ኦሪት ሕግ መምህራን ዝነኛ ለመ
ሆን ይመኛሉ። ይሁን እንጂ ስለ ሕጉ የሚ
ያስተምሩትንም ሆነ የሚያምኑትን አጥር
ተው አያውቁም። [8] ሕግ ሰዎች በትክክል
ከተጠቀሙበት መልካም ነገር ነው። ይህን
ንም ስል ፣ ሕግ የተሰጠው በአግባብና በሥነ
ሥርዓት ለሚኖሩ ሰዎች እንዳልሆነ መረ
ዳት ያስፈልጋል። [9] ሕግ የተሰጠው ለወንጀ
ለኞች ፣ ለአመፀኞች ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር
ለሌላቸውና ለኃጢአተኞች፣ለርኩሳንና ለእ
ምነተ ቢሶች ፣ አባትና እናታቸውን ለሚገ
ድሉ ፣ ለነፍሰ ገዳዮች ፣ [10-11] ለአመንዝሮች ፣
ግብረ ሰዶም ለሚፈጽሙ ፣ በሰዎች ለሚነ

ግዱ ፥ ለውሸተኞችና ፥ ለቃለ አባዮች፥በጠቅላ
ላውም ከእውነተኛው ትምህርት ተቃራኒ
የሆነውን ነገር ለሚፈጽሙ ሁሉ ነው።
እውነተኛው ትምህርት የሚገኘውም ፥ እኔ
እንዳስተምረው አደራ በተሰጠኝና የእግዚአ
ብሔርን ታላቅ ክብር በሚገልጸው በወን
ጌል የምሥራች ቃል ነው።
12 በአገልግሎቴ ብርታት ለሰጠኝና
ታማኝ አደርጎ ስለቆጠረኝም መልእክተ
ኛው እንድሆን ለመረጠኝ ፥ ለጌታዬ ለኢየ
ሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይድረሰው። 13 ከዚህ
በፊት በክርስቶስ ላይ የዘበትኩበትና በእር
ሱም የሚያምኑትን ያሳደድሁ አመፀኛ ሰው
ብሆንም እንኳን ፥ ይህን ሁሉ አደርግ የነበ
ረው ካለማወቅና ካለማመን የተነሣ ስለነ
በር ፥ እግዚአብሔር በደሌን ሁሉ ይቅር
ብሎ ምሮኛል። 14 ጌታ ግን ምንኛ ቸር
ነው? በክርስቶስ ኢየሱስ ባገኘሁት እምነ
ትና ፍቅር ላይ ጨምሮ ፥ የተትረፈረፈ ጸጋ
ውን አበዛልኝ።
15 በእርግጥም ፥ «ኃጢአተኞችን ለማ
ዳን ክርስቶስ ወደ ዓለም መጣ» የሚለው
ቃል እውነተኛ ነው። ሰው ሁሉ የዚህን
ቃል እውነተኛነት ተረድቶ ሊቀበለው ይገ
ባል። እኔ ከኃጢአተኞች ሁሉ የምበልጥ
ኃጢአተኛ ነበርኩ። 16 እግዚአብሔር እን
ዲህ አድርጎ ምሕረቱን ያሳየኝ ፥ የሰው
ልጆች ሁሉ ክርስቶስ እንደ እኔ ላለ
ኃጢአተኛ ምን ያህል ትዕግሥት እንዳ
ለው እንዲረዱና እነርሱም እንደ እኔ
አምነው የዘላለምን ሕይወት ሊያገኙ እን
ደሚችሉ ለማሳወቅ ነው። 17 ስለዚህ ዘላለ
ማዊ ንጉሥ ለሆነው፥በዓይን ለማይታየውና
ምን ጊዜም ለማያልፈው ለአንዱ አምላክ
ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብርና ምስጋና
ይሁን፤አሜን።
18 ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ ፥ ይህ አሁን
የምመክርህ ቃል አስቀድሞ ስለአንተ በትን
ቢት በተነገረው መሠረት ነው። ይህንንም
የትንቢት ቃል በማስተዋል ፥ መልካሙን
መንፈሳዊ ውጊያ ተዋጋ። 19 በክርስቶስ ያለ
ህን እምነት አጥብቀህ ያዝ። ንጹሕ ሕሊ
ናም ይኑርህ የምታደርገው ነገር ሁሉ ትክ
ክለኛ ይሁን። አንዳንድ ሰዎች የኅሊናቸ
ውን ወቀሳ እንቀበልም በማለታቸው እያ
ወቁና ወደው ኃጢአትን በመፈጸም እም
ነታቸው ተንኮታኩቶ እንዲወድቅ አድርገ
ዋል። 20 ለዚህ ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ
ጥሩ ምሳሌ ናቸው። እነርሱ የክርስቶስን
ስም ማዋረድ እስኪያቆሙ ድረስ ቅጣታ
ቸውን እንዲቀበሉ ለሰይጣን አሳልፌ ሰጥ
ቻቸዋለሁ።

## ምዕራፍ 2

1 ከሁሉ አስቀድሞ ስለ ሰዎች ሁሉ በእ
ግዚአብሔር ፊት ልመና ፥ ጸሎትና ምልጃ
እንዲደረግ ፥ ምስጋናም እንዲቀርብ እመክራ
ለሁ።
2 ጌታን በመፍራትና በማምለክ በጸጥታና
በሰላም ለመኖር እንድንችል ፥ ለርእሰ ብሔ
ሮች ፥ ለባለሥልጣናትና በኃላፊነት ላይ
ላሉ ሁሉ መጸለይ ይገባናል። 3 ይህንን
መፈጸም መልካምና ጌታችንንም የሚያስ
ደስት ነገር ነው። 4 ምክንያቱም ሰዎች
ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ማወቅ እንዲ
ችሉ አዳኛችን እግዚአብሔር ይፈልጋ
ልና። 5 አንድ እግዚአብሔር አለና፤በሰዎ
ችና በእግዚአብሔር መካከል ዕርቅን ማስገ
ኘት የሚችልም አንድ ብቻ ነው፤እርሱም
ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 6 ክር
ስቶስ ሕይወቱን ለሰዎች ሁሉ ኃጢአት ቤዛ
አድርጎ አቀረበ። ይህም እግዚአብሔር
ሰዎችን ለማዳን እንደሚፈልግ በተገቢው
ወቅት የታወጀ ማረጋገጫ ነው። 7 እኔም
ይህንን ትክክለኛ እምነት ለአሕዛብ እንዳስ
ተምር ሐዋርያና የምሥራች ነጋሪ ሆኜ
ተመረጥኩ። እውነቱን እናገራለሁ አልዋ
ሽም።
8 ስለዚህ በየቦታው የሚገኙ ወንዶች
ሁሉ ከኃጢአትና ከቁጣ ነፃ ሆነው፥በቅድ
ስና እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው እን
ዲጸልዩ እፈልጋለሁ። 9-10 ሴቶች ደግሞ በጸ
ጥታና በርጋታ በአለባበስም በጠባይም
ጨምተው መገኘት ይገባቸዋል። ክርስቲያን
ሴቶች መታወቅ የሚገባቸው በዘመናዊ አለ
ባበሳቸው፥በጌጣ ጌጣቸውና በጠጉር አሠራ
ራቸው ሳይሆን፥በጨዋነታቸውና በደግነታ
ቸው መሆን አለበት። 11 እንዲሁም ሴቶች
ትሕትና በተመላበትና ረጋ ባለ መንፈስ
መማር አለባቸው።
12 ሴት ወንድን እንድታስተምር ወይም
እንድትገዛ አልፈቅድም። እርስዋ መጨመ
ትን መማር አለባት። 13 ምክንያቱም እግዚ
አብሔር በመጀመሪያ አዳምን ፥ ቀጥሎም
ሔዋንን ፈጥሯል። 14 ደግሞም በመጀመሪያ
በሰይጣን የተታለለው አዳም ሳይሆን በመጀ
መሪያ የተታለለችውና ኃጢአትን የሠራ
ችው ሔዋን ነበረች። 15 ሆኖም ሴት በጸጥ
ታና በጥሞና፥በእምነት፥በፍቅርና በቅድስና
ከኖረች ልጅ በመውለድ ትድናለች።

## ምዕራፍ 3

1 የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን የሚያ
ስብ ሰው መልካም አገልግሎትን ተመኝ
ቷል ማለት ይቻላል። 2 የቤተ ክርስቲያን
መሪ መሆን የሚገባው ሰው፣የሚነቀፍ ነገር
የሌለበት ፤ የአንዲት ሚስት ባል ፣ ትጉሕና
ጠንካራ ሠራተኛ መሆን ይገባዋል። እንዲ
ሁም በሥርዓት የሚኖር ፣ በመልካም ተግ
ባሩ የታወቀ፣እንግዶችን የሚቀበልና የሚያ
ስተናግድ ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተ
ማር ችሎታ ያለው ፣ 3 የማይሰክር ፣ ጸበኛ
ያልሆነ፣ደግና ጨዋ የሆነ፣ለገንዘብ የማይስ
ገበገብ ፣ 4 ቤቱን በመልካም ሥነ ሥርዓት
የሚያስተዳድርና የሚታዘዙ ልጆች ያሉት
መሆን ይገባዋል። 5 አንተስ ስታስበው የራ
ሱን ቤተ ሰብ ማስተዳደር ያልቻለ ሰው፣የእ
ግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊያ
ስተዳድር ይችላል?

6 በተጨማሪም ቶሎ በመሾሙ ኩራት
ተሰምቶት እንደ ሰይጣን በተመሳሳይ ፍርድ
ውስጥ እንዳይወድቅ፣አዲስ ያመነ ክርስቲ
ያን ለመሪነት መመረጥ የለበትም። 7 ይህን
በመሰለው የኃላፊነት ሥራ ላይ የሚመደብ
ሰው ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ካሉ ሰዎች
ዘንድም ጥሩ ምስክርነት ያለው ሊሆን ይገ
ባል። ምክንያቱም ሰይጣን ከየአቅጣጫው
ነቀፋና ክስ በማስነሣት፣አደራ የተጣለበትን
ምዕመናን የማስተዳደር ነፃነት እንዳያሳ
ጣው ስለሚያሠጋ ነው።

8 ዲያቆናትም በሚመረጡበት ጊዜ እንደ
ዚሁ ጥሩ ምስክርነት ያላቸው መሆን አለባ
ቸው። በተጨማሪም ቅኖች ፣ የማይሰክሩና
ለጥቅም የማይስገበገቡ ሊሆኑ ይገባል።
9 ከዚህም ሌላ፣ዲያቆናት የእምነትን ምሥ
ጢር በንጹሕ ሕሊና የሚጠብቁ መሆን ይገ
ባቸዋል። 10 ከመመረጣቸውም አስቀድሞ
ጠባያቸውና ችሎታቸው መፈተንና መታ
የት ይኖርበታል። በአኗኗራቸውና በአካሄዳ
ቸው ምንም ነቀፋ የሌለባቸው ሆነው ከተ
ገኙ ለዲቁና ይመረጡ።

11 እንዲሁም የዲያቆናት ሚስቶች ጠባ
ዎችና ሐሜተኞች ሳይሆኑ ፣ በማንኛውም
መንገድ ጨዋዎችና ታማኞች ፣ መልካም
ምስክርነትም ያላቸው ይሁኑ። 12 ዲያቆን
የአንዲት ሚስት ባል ሆኖ ፣ ልጆቹንና ጠቅ
ላላ ቤተ ሰቡን በሥርዓት የሚያስተዳድር
መሆን ይገባዋል።

13 በዲቁና ሥራቸው የተጣለባቸውን
አደራ በሚገባ የሚፈጽሙ ክብር ያገኛሉ።
በክርስቶስ ላይ ያላቸው መታመንና የራሳቸ
ውም ብቃት፣እያደገና እየዳበረም ይሄዳል።

14 ምንም እንኳ በቅርቡ እንደማይህ
ተስፋ ባደርግም ይህንን መልእክት ጽፌልሃ
ለሁ። 15 ምክንያቱም፣ምናልባት ወደ አንተ
ሳልመጣ ጥቂት ጊዜ ብዘገይ፣የእውነት ዓም
ድና መሠረት በሆነው የሕያው እግዚአብ
ሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣እንዴት ማገል
ገልና መኖር እንደሚገባ እንድታውቅ ብዬ
ነው።

16 የሃይማኖታችን ምሥጢር እጅግ
ጥልቅ መሆኑን ማንም ሊክድ አይችልም።
የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋን ለብሶ ወደ
ምድር መጣ፣የመንፈስ ንጽሕናውና ትክክለ
ኛነቱ ነቀፋ የሌለበት መሆኑ ተመሰከረለት፣
ለመላእክት ታየ፤ስለ እርሱ የተነገረው የም
ሥራች ቃል ለሕዝብ ሁሉ ተሰበከ፤በዓለም
ዙሪያ የሚገኙ ሰዎች አምነው ተቀበሉት፤
በክብርም ወደሰማይ ወጣ።

## ምዕራፍ 4

1 መንፈስ ቅዱስ ግን በመጨረሻው
ዘመን አንዳንዶች የሰይጣንን አሳብ ተከት
ለው ክርስቶስን በመካድ የሐሰት ትምህርት
እንደሚቀበሉ ነግሮናል። 2 ይህንን የሐሰት
ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ሁልጊዜ
በግብዝነት ውሸትን የሚናገሩና ለሚያደር
ጉት ስሕተትም የሕሊና ወቀሳ የማይሰማ
ቸው ናቸው። 3 መጋባትን ይከለክላሉ፤እም
ነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ የጣሉ፣እር
ሱም የገለጠላቸውን እውነት የተረዱ ሰዎች
በምስጋና እንዲቀበሉት የፈጠረላቸውን
ምግብ ፣ ‘አትብሉ’ እያሉ ይከለክላሉ።
4 እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ መል
ካም ነው። ለእግዚአብሔር ምስጋና ሰጥተን
ከበላነው ተንቆ የሚጣል አንዳችም የምግብ
ዓይነት የለም። 5 በእግዚአብሔር ቃልና በጸ
ሎት ተቀድሷልና።

6 ስለዚህ ጉዳይ ለምዕመናን አብራርተህ
ብታስተምር በመልካም ትምህርትና በጽኑ
እምነት የታነጽህ፣መልካም የክርስቶስ ኢየ
ሱስ አገልጋይ መሆንህን ታስመሰክራለህ።

7 ጊዜህን መንፈሳዊ ሕይወትህ ሊያድግና
ሊዳብር በሚችልበት ነገር ላይ አውል
እንጂ ፣ ከቧልተኞችና ረብ የለሽ የሞኞች
ታሪክ እያነሡ ከሚከራከሩ ሰዎች ጋር አታ
ባክነው። 8 የሰውነት ማጠንከሪያ ለአካል
መጠነኛ ጥቅም ይሰጣል። መንፈሳዊነት
ግን ለሁሉ ነገር ይጠቅማል። ራስን በመንፈ
ሳዊ ነገር እንዲዳብር ማድረግ ለዚህ ሕይ

ወት ብቻ ሳይሆን፣ለሚመጣውም ሕይወት
ጭምር ተስፋ አለው። 9 ይህ የማያጠራጥ
ርና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባው እው
ነት ነው። 10 እኛም የምንለፋውና የምንታ
ገለው ለዚህ ሕይወት ነው። ይህንንም የም
ናደርገው የሰው ሁሉ፣በተለይም የአማኞች
አዳኝ በሆነው በሕያው እግዚአብሔር ላይ
እምነታችንን ጥለን ነው።

11 እነዚህን ነገሮች ለሚሰሙህ ሁሉ
በሚገባ ተረድተው እስኪቀበሏቸው ድረስ
ሳትታክት አስተምራቸው። 12 ገና ወጣት
በመሆንህ ማንም አይናቅህ። የምታስተምረ
ውን ትምህርት በንግግርህ፣በኑሮህ፣በፍቅ
ርህ፣በእምነትህና በንጹሕ አካሄድህ እያሳ
የህ፣ለምዕመናን ሁሉ ምሳሌ ሁን። 13 እስክ
መጣ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝብ
እያነበብክ፣እየሰበክህና እያስተማርክ ጠብ
ቀኝ።

14 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እጃቸ
ውን በራስህ ላይ ጭነው በጸለዩልህ ጊዜ፣
በትንቢት ቃል አማካይነት የተሰጠህን መን
ፈሳዊ ስጦታ ቸል ሳትል ሥራበት።
15 ሰዎች ሁሉ የሥራህን ውጤትና ዕድገት
እንዲያዩ፣ለነዚህ ከላይ ለጠቀስኩልህ ነገ
ሮች ራስህን ሙሉ ለሙሉ በመስጠት በአገ
ልግሎትህ ትጋ። 16 በምታደርገው ሆነ በም
ታስተምረው ነገር ሁሉ ጥንቃቄ አይጉደ
ልህ። ለሌሎች በምታስተምረው ትምህርት
ላይ አንተ ራስህ የጸናህ ሁን። ይህን ብታደ
ርግ፣ራስህንም ሆነ የሚሰሙህን ሁሉ ታድ
ናለህ።

## ምዕራፍ 5

1 ሽማግሌዎችን እንደ አባት በመቁጠር
በአክብሮት አስረዳቸው እንጂ በቁጣ አትና
ገራቸው። ወጣት ወንዶችንም እንደ ታና
ናሽ ወንድሞችህ በመቁጠር በፍቅር ያዛ
ቸው። 2 በዕድሜ ጠና ያሉትን ሴቶች እንደ
እናቶችህ፣ወጣት ሴቶችን እንደ እኅቶችህ
በመቁጠር፣በንጽሕና ተንከባከባቸው።

3 ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ብቸኞች
ሴቶች የሚገባውን እንክብካቤ አድርግላ
ቸው። 4 ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ካሏ
ቸው ግን፣እነርሱ አስፈላጊውን እርዳታ
የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው እንዲያው
ቁት ያስፈልጋል። ክርስቲያናዊ በጎ ምግባር
መጀመር ያለበትም አቅመ ደካማ የሆኑ
ወላጆችን በመርዳትና ውለታቸውን በመመ
ለስ ነው። እንዲህ ያለው በጎ ሥራ እግዚአ
ብሔርን ደስ ያሰኘዋል።

5 ባልዋ የሞተባት ብቸኛ ሴት ተስፋዋን
ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ አድርጋ ቀንና
ሌሊት በጸሎት ትተጋለች። 6 የዚህን ዓለም
ደስታ የምትሻዋ ግን፣በቁምዋ ሳለች የሞ
ተች ናት። 7 በዚህ ነገር ማንም ነቀፋ እንዳ
ይገኝበት ይህን መመሪያ ምዕመናን ሁሉ
ይወቁት።

8 በችግር ላይ የሚገኙትን ዘመዶቹን
በተለይም የራሱን ቤተ ሰብ የማይረዳ ነገር
ግን፣ 'ክርስቲያን ነኝ' የሚል ሰው ቢኖር፣
እርሱ እምነቱን የካደና ከማያምኑ ሰዎች
ይልቅ የከፋ ነው።

9 ባል የሞተባት ሴት በቤተ ክርስቲያን
የመበለቶች መዝገብ ውስጥ ለመመዝገብ፣
ዕድሜዋ ስድሳ ዓመት የሞላና አንድ ባል
ብቻ የነበራት መሆን ይኖርባታል። 10 እንዲ
ሁም በመልካም ተግባሯ የተመሰከረላት
ማለትም፣ልጆቿን በሚገባ ያሳደገች፣እንግዳ
ተቀባይ፣ከመንገድ ደክመው የገቡ ክርስቲያ
ኖችን እግር በማጠብ ትሕትና ያሳየች፣ችግ
ረኞችን በመርዳትና በማንኛውም በጎ ሥራ
ተሳትፎ ያደረገች መሆን ይኖርባታል።

11 ባል የሞተባቸው ወጣት ሴቶች ግን
በመበለቶች መዝገብ ውስጥ ለመግባት ቢፈ
ልጉ አትፍቀድላቸው። ምክንያቱም እነርሱ
ጌታን በሙሉ ልብ ለማገልገል የገቡትን
ቃል ኪዳን አፍርሰው ለሥጋዊ ስሜታቸው
በመሸነፍ፣እንደገና ለማግባት መፈለጋቸው
አይቀርምና። 12 እንደዚህ ያሉት ሴቶች
ተስፋ የገቡለትን የመጀመሪያ ቃላቸውን
በማጠፋቸው በቃል ኪዳን አፍራሽነታቸው
ይፈረድባቸዋል። 13 ከዚህም በቀር ከቤት
ወደ ቤት በመዞርና በሰው ነገር ጣልቃ
በመግባት በሐሜትና ስም በማጥፋት ጊዜያ
ቸውን በስንፍና ያጠፋሉ። 14 እንደ እኔ
ከሆነ እነዚህን የመሰሉት ወጣት ሴቶች
በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መበለት ሆነው
ለመኖር ከመወሰን ይልቅ እንደገና ቢያገቡ፣
ልጆች ቢወልዱና ቤታቸውን በጥንቃቄ
ቢይዙ ይሻላል። እንዲህ ከሆነ ጠላት ዲያብ
ሎስ ሊነቅፋቸው የሚችልበት ነገር አያገኝ
ባቸውም። 15 ይህንንም የምለው፣ ከዚህ
በፊት በሰይጣን የተታለሉና ከቤተ ክርስቲ
ያን ርቀው የሄዱ አንዳንዶች ሴቶች እንዳሉ
ስለማውቅ ነው።

16 አማኞች ባል የሞተባቸው ሴቶች
ዘመዶች ካሏቸው፣ሊረዷቸውና ሊያስቡላ
ቸው ይገባል። እንዲህ ያለው ተግባር የቤተ
ክርስቲያን ኃላፊነት ነው በማለት የእርዳታ
እጃቸውን ማጠፍ የለባቸውም። ምክንያ

ቱም ቤተ ክርስቲያን ባሎቻቸው የሞቱባቸ
ውን፥ምንም ረዳት የሌላቸውን ሴቶች ብቻ
መንከባከብ ስለሚገባት ነው።
[17]ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያስተዳ
ድሩና በተለይም ወንጌልን በመስበክና በማ
ስተማር የሚደክሙ መሪዎች በቂ ደሞዝ
ሊከፈላቸው ይገባል። [18]ምክንያቱም መጽ
ሐፍ፥ «እህል የሚያበራየውን በሬ አፉን
አትሠር ፤ እየሠራ ሳለ ይብላ» ይላልና።
በሌላ ቦታ ደግሞ፥ «ለሠራተኛ የላቡ ዋጋ
ሊከፈለው ይገባል» ተብሎ ተጽፏል።
[19]ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ካል
መሰከሩበት በቀር በቤተ ክርስቲያን መሪ
ላይ የሚቀርበውን ክስ አትቀበል።
[20]ሆኖም ኃጢአት ማድረጉ የተረጋገጠ
ሆኖ ከተገኘ ግን፥የእርሱን መጥፎ አርአያ
ሌሎች እንዳይከተሉ በምዕመናን ፊት ይገ
ሠጽ።
[21]ማንኛውንም ሰው አንዱን ከሌላው
ሳታበላልጥ ይህንን የነገርኩህን መመሪያ
ሁሉ ያለ አድልዎ እንድትፈጽም በእግዚአ
ብሔር፥በክርስቶስ ኢየሱስ ፊትና በቅዱሳን
መላእክት ፊት አደራ እልሃለሁ። [22]ለቤተ
ክርስቲያን መሪነት ለመሾም፥በማንም ሰው
ላይ በችኰላ ተነስተህ እጅህን አትጫን።
የሰውየውን ጠባይ ሳትመረምር ሾመህ
አንተ ራስህ የከፋ ሥራው ተባባሪ ሆነህ
እንዳትገኝ። ስለዚህ አንተም ብትሆን ራስ
ህን በንጽሕና ጠብቅ።
[23]እየደጋገመ ለሚነሣብህ የሆድ ሕመ
ምህ ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት እንጂ
ውኃ ብቻ አታዘውትር።
[24]የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት ለሁሉም
ግልጽ ሆኖ ይታያል ፤ የሚመጣባቸውንም
ፍርድን ያመለክታል። የሌሎች ሰዎች ኃጢ
አት ደግሞ ኀልቶ የሚታየውና ይፋ የሚወ
ጣው፥ ውሎ አድሮ ነው። [25]እንደዚሁም
መልካም ሥራ ሁሉ በግልጽ ይታወቃል።
ለጊዜው ያልታወቀውም ሁሉ ተደብቆ አይ
ቀርም።

## ምዕራፍ 6

[1]«እነዚህ ክርስቲያኖች ልግመኞች
ናቸው» በመባል የእግዚአብሔርን ስምና
የእኛን ትምህርት እንዳያስነቅፉ፥ክርስቲያን
አገልጋዮች ሁሉ የቤት አሳዳሪዎቻቸውን
መታዘዝና ማክበር ይገባቸዋል። [2]አሳዳሪዎ
ቻቸው ክርስቲያኖች ከሆኑ በክርስቶስ ወን
ድሞቻቸው በመሆናቸው ምክንያት የሚገባ
ቸውን ክብር ሊነፍጓቸው አይገባም። ይል
ቁንም እነዚህን አማኝና የተወደዱ አሳዳሪ
ዎቻቸውን ከፊት የበለጠ ሊያገለግሏቸው
ያስፈልጋል። ከልባቸው ሊያገለግሉት ይገ
ባል። ይህንን በሚገባ ማስተማርና በሥራ
ላይ እንዲውል ማድረግ አለብህ።
[3]አንዳንዶች በመታበይ ይህንን ትምህ
ርት አንቀበልም ይሉ ይሆናል። ይሁን
እንጂ ይህ ትምህርት ለመንፈሳዊ ሕይወት
መሠረት ሊሆን የሚችል የጌታችን የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ትክክለኛ ትምህርት ነው።
[4]ከዚህ የተለየ አሳብ ያለው ቢኖር፥እርሱ
ትዕቢተኛና የማይጠቅም ሰው ነው። ምክን
ያቱም እንዲህ ያለው ሰው የክርስቶስን ቃል
በማጣመም ቅንዓትን፥ስድብን፥ቁጣን፥ጥርጣ
ሬን የሚያስከትል ክርክር ይቀሰቅሳል።
[5]እንደዚህ ያለው ሰው አእምሮው በኃጢ
አት የተበከለ በመሆኑ እውነትን የተቀማ
ነው። ለእርሱ ሃይማኖት የጥቅም ማግኛ
መሣሪያ መስሎ ይታየዋል።
[6]'ያለኝ ይበቃኛል' ለሚል ሰው ግን፥
ሃይማኖት ትልቅ ሀብት ነው። [7]ወደዚህ
ዓለም ገንዘብ ቋጥረን አልመጣንም። ከዚህ
ዓለም በሞት በምንለይበትም ጊዜ ቤሳቤስ
ቲን ይዘን አንሄድም። [8]ስለዚህ የምንበላ
ውና የምንለብሰው ካለን፥ትርፍ ገንዘብ ባይ
ኖረንም፥ረክተንና ተደስተን መኖር እንችላ
ለን። [9]ሀብታሞች ለመሆን የሚጓጉ፥ያንን
የሚጓጉለትን ገንዘብ ለማግኘት ነፍሳቸውን
በሚጐዳ ፈተና፥ወጥመድና ልዩ ልዩ ክፉ
ምኞት ውስጥ ይወድቃሉ። [10]ምክንያቱም
የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ
ነውና። አንዳንድ ሰዎች ከገንዘብ ፍቅር የተ
ነሣ በእግዚአብሔር ላይ እንኳን ፊታቸውን
አዙረዋል። በዚህ ምክንያት ሕይወታቸው
በብዙ ኀዘን የተጐሳቀለ ሆኗል።
[11]ጢሞቴዎስ ሆይ፥አንተ ግን የእግዚአ
ብሔር ሰው ስለሆንክ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ
ራቅ። መልካም የሆነውን ነገርና መንፈሳዊ
ነትን፥ፍቅርን፥በጌታ መታመንን፥ጨዋነት
ንና ትዕግሥትን ተከተል። [12]መልካሙን
የእምነት ውጊያ ተዋጋ። በብዙ ሰዎች ፊት
እምነትህን ባስታወቅህበት ጊዜ ከእግዚአብ
ሔር የተሰጠህን የዘላለምን ሕይወት ስጦታ
አጥብቀህ ያዝ። [13]ለሰው ሁሉ ሕይወትን
በሚያድለው በእግዚአብሔርና በጴንጤና
ዊው ጲላጦስ ፊት ያለ ፍርሃት ምስክርነ
ቱን በሰጠው በክርስቶስ ስም፥ [14]ከአሁን
ጀምሮ ጌታ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ፥
ያለ ምንም ነቀፋ ይህን ትእዛዝ በመፈጸም
እንድትኖር አደራ እልሃለሁ። [15]የጌቶች

ጌታና የነገሥታት ንጉሥ፣ 16 ምን ጊዜም
የማይሞተው፣ ማንም ፍጡር ሊደርስበት
በማይችል ብርሃን ውስጥ የሚኖረው፣ማንም
ሰው ያላየውና ሊያየውም የማይችለው
አንድ አምላክ፣ እርሱ ራሱ በወሰነው ጊዜ
ክርስቶስ ይገለጣል። ለእርሱ ክብር፣ኃይልና
ግዛት ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤
አሜን።

17 ሀብታሞችን እንዳይኰሩና አላፊና
ጠፊ በሆነው በዚህ ዓለም ሀብት እንዳይታ
መኑ ምከራቸው። ነገር ግን፣ደስ እንሰኝበት
ዘንድ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደባለጸግነቱ
መጠን በሚሰጠን፣ በእግዚአብሔር ብቻ
ይታመኑ። 18 ደግሞም በገንዘባቸው መል
ካም ማድረግን እንዲማሩ፣ለችግረኞች እንዲ
ቸሩ፣እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሀብት ከሌ
ሎች ጋር መካፈልን እንዲያውቁ ምከራ
ቸው። 19 እንዲህ የሚያደርጉ ከሆነ እውነ
ተኛውን ሕይወት ያገኙ ዘንድ ለዘላለም
የሚቆይ ሀብት በሰማይ በማከማቸት፣ለሚ
መጣው ዓለም መልካም መሠረትን ለራሳ
ቸው ያኖራሉ።

20 ጢሞቴዎስ ሆይ፣ጌታ የሰጠህን አደራ
ጠብቅ። በእውቀታቸው ከሚመኩ ሰዎች
የሞኝነት ክርክር ራቅ። 21 ምክንያቱም አን
ዳንድ ሰዎች በዚህ ዓይነቱ የሐሰት እው
ቀት ተታለው ከእውነተኛው እምነት
ርቀው ሄደዋል።

የእግዚአብሔር ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን።

መንፈሳዊ አባትህ
ጳውሎስ

## ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለጢሞቴዎስ የጻፈው ሁለተኛው መልእክት

### መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፣ የተጻፈበትም ዘመን በ64 ዓ.ም. እንደሆነ ይገመታል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ወንጌልን በማስተማሩ ምክንያት እንደገና ተይዞ በታሠረበትና ፍርዱን በሚጠባበቅበት ወቅት ነበር። ይህ ታላቅ ሐዋርያ ለጢሞቴዎስ በላከው በዚህ የአደራ መልእክቱ፣በእግዚአብሔር መንፈስ አነቃቂነት የተጻፉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል፣ ሰዎች የማይቀበሉበት ዘመን የሚመጣ መሆኑን ገልጾ፣እርሱ ግን ነቅቶና ተግቶ እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያስተምር አበክሮ ያሳስበዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ የዘ
ላለም ሕይወትን እንደሚያገኙ ስለ ተሰ
ጠው ተስፋ እንዲያስተምር፣ እግዚአብሔር
መልእክተኛ አድርጎ ከሾመው ከጳውሎስ
የተላከ።

2 የተወደድከው ልጄ ጢሞቴዎስ፣ የእግ
ዚአብሔር አባታችን፣ የጌታችንም የኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋ፣ምሕረትና ሰላም ይብዛልህ።

3 ቀንም ሆነ ሌሊት በተንበረከክሁ ቁጥር
በጸሎቴ አስታውስሃለሁ። እንደ አባቶቼ በን
ጹሕ ሕሊና የማገለግለውን እግዚአብሔር
ንም፣ ስለ አንተ ከልቤ አመሰግነዋለሁ።
4 እንደገና ዓይን ለዓይን ብንገናኝ እንዴት
ደስ ባለኝ! በተለያየንበት ጊዜ፣ ያፈሰስከው
እንባ አሁንም ከፊቴ መጥቶ ድቅን ይላል።
5 ልክ እንደ እናትህ እንደ ኤውንቄና እንደ
አያትህ እንደ ሎይድ፣ እውነተኛ እምነት
ያለህ ሰው መሆንህን አውቃለሁ።

6 ስለዚህ እጆቼን በአንተ ላይ ጭኜ በጸለ
ይኩልህ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠህ መንፈ
ሳዊ ስጦታ እንዳይዳፈን፣ አቀጣጥለህ እንድ
ትሠራበት አሳስብሃለሁ። 7 ከእግዚአብሔር
የተቀበልከው ይህ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል
ፍርሃትን ያስወግድልሃል። ሰዎችን የምታፈ
ቅርና ራስህን መግዛት የምትችል ጠቢብና
ጠንካራ ሠራተኛም ያደርግሃል። 8 ስለ ጌታ

ችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር አት
ፈር። እኔም ስለ እርሱ በመታሠሬ ሐፍረት
አይሰማህ። እግዚአብሔር በሚሰጥህ ኃይል
በመተማመን በወንጌል ምክንያት የሚመጣ
ውን ችግር ሁሉ ከጎኔ ቆመህ ለመቀበል
ተዘጋጅ።
[9] በእኛ ብቃት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር
ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በክርስቶስ ባቀደል
ንና በሰጠን በጸጋው አዳነን። ለዚህ ለተቀ
ደሰ አገልግሎትም መረጠን። [10] ሞትን ድል
ነሥቶ የዘላለምን ሕይወት ያስገኘልን ክርስ
ቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ፥ እግዚአብ
ሔር ከዘመናት በፊት ለእኛ ያቀደውን
ጸጋ፥ በእርሱ አማካይነት አደለን። [11] እኔም
ይህንን የምሥራች እንድናገር እግዚአብሔር
ሐዋርያና አስተማሪ አድርጎ መርጦኛል።
[12] በአሁኑ ጊዜ በእሥር ቤት ውስጥ
በመሠቃየት ላይ የምገኘው በዚህ ምክንያት
ነው። ይሁን እንጂ በመታሠሬ አላፍርበ
ትም። ምክንያቱም ያመንሁት ማንን እንደ
ሆነ አውቃለሁ። እርሱም ተመልሶ ወደ
ምድር እስከሚመጣበት ቀን ድረስ የሰጠሁ
ትን አደራ ሊጠብቅ እንደሚችል እርግጠኛ
ነኝ።
[13] ከእኔ የተማርከውን እውነት በክርስ
ቶስ ከሚገኘው እምነትና ፍቅር ጋር አዋሕ
ደህ እንደመመሪያህ ያዘው። [14] በአደራ የተ
ሰጠህን አገልግሎት በውስጥህ ባደረው በመ
ንፈስ ቅዱስ ኃይል ደህና አድርገህ ጠብ
ቀው።
[15] እንደምታውቀው ፥ በታናሹ እስያ
ያሉት ክርስቲያኖች ሁሉ ከድተውኛል።
ፊሎጎስና ሄርሞጌኔስ እንኳ ሳይቀሩ ትተው
ኛል። [16] ነገር ግን እግዚአብሔር ሄኔሲፎሩ
ንና ቤተ ሰቡን ይባርካቸው። ምክንያቱም
እርሱ በመታሠሬ ሳያፍር ብዙ ጊዜ መጥቶ
በመጠየቅ አጽናንቶኛል። [17] ወደ ሮም
በመጣ ጊዜም እኔን ለማግኘት ብዙ ደክሞ
አል። [18] ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ በሚመጣ
በት ቀን ዋጋውን ይክፈለው። በኤፌሶን በነ
በርኩበትም ጊዜ ይህ ወንድም ምን ያህል
እንደ ረዳኝ ታውቃለህ።

## ምዕራፍ 2

[1] ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ፥የጌታ ጸጋ ያበር
ታህ። [2] በብዙ ምስክሮች ፊት ያስተማርኩ
ህን ቃል አንተም መልሰህ፥ሌሎችን ማስተ
ማር ለሚችሉ ብቁና ታማኝ ለሆኑ ሰዎች
አስተምር።
[3] የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ወታደር
በመሆን መከራን ተቀበል። [4] የክርስቶስ
ወታደር በመሆንህ በዚህ ዓለም ጣጣ ራስ
ህን መተብተብ የለብህም። ምክንያቱም እን
ዲህ ካደረግህ የጦር መሪህን ክርስቶስን ለማ
ስደሰት አትችልምና። [5] የስፖርትን ሕግ
በመከተል የማይወዳደር ስፖርተኛ በተሰለ
ፈበት ውድድር አሸንፎ ሽልማት መቀበል
አይችልም። አንተም የጌታን ቃል በመከ
ተል የተሰጠህን ሥራ በትጋት ፈጽም።
[6] ደክሞ ያረሰ ገበሬ የድካሙን ዋጋ እንደ
ሚያገኝ በማወቅ በትጋትና በጥንካሬ ሥራ።
[7] እነዚህን ምሳሌዎች ልብ ብለህ አስተ
ውል። የምሳሌዎቹ ምሥጢር ምን እንደ
ሆነ እንድታስተውል ጌታ ራሱ እንደሚረ
ዳህ አምናለሁ። [8] ከሞት የተነሣውንና ከዳ
ዊት ዘር የሆነውን፥እኔም የምሰብከውን ኢየ
ሱስ ክርስቶስን አስብ። [9] በአሁኑ ጊዜ እኔ
እንዲህ በችግርና በእሥር ላይ የምገኘው
ይህንን ታላቅ እውነት በማስተማሬ ብቻ
ነው። እኔ ብታሠርም የእግዚአብሔር ቃል
ሊታሠርና ሊገታ አይችልም። [10] እግዚአብ
ሔር የመረጣቸው ደግሞ በክርስቶስ ኢየ
ሱስ ደኅንነትንና የዘላለምን ክብር እንዲያ
ገኙ፥ስለ እነርሱ ማንኛውንም ሥቃይ በትዕ
ግሥት ለመቀበል ፈቃደኛ ነኝ።
[11] ይህ የታመነ ቃል ነው። ከክርስቶስ
ጋር ብንሞት ከእርሱ ጋር ሕያዋን ሆነን
እንደምንኖር በማወቁ እጽናናለሁ። [12] በትዕ
ግሥት ከእርሱ ጋር ጸንተን ከቆየን አብረ
ነው የምንነግሥ መሆናችንን እናውቃለን።
መከራን በመፍራት ክርስቶስን ብንክደው
ግን ፥ እርሱም ይክደናል። [13] እኛ ታማኝ
ሆነን ባንገኝ ፥ እርሱ ምን ጊዜም ቢሆን
ታማኝ ሆኖ ይኖራል። እርሱ ራሱን ሊክድ
አይችልምና።
[14] ክርስቲያኖች ይህንን እውነት እንዳይ
ዘነጉ አስታውሳቸው። እንዲሁም በማይረባ
ነገር እንዳይከራከሩ በእግዚአብሔር ፊት
ተቆጣቸው። ምክንያቱም በማይረባ ነገር
መከራከር ጥቅም የሌለውና በጣምም ጎጂ
ነገር ነው። [15] የእግዚአብሔርን ቃል ምሥ
ጢር በማወቅና በትክክል በማስተማር የማ
ታሳፍር ሠራተኛ መሆንህን ለማሳየት፥በእግ
ዚአብሔር ፊት ትጋትህ እጥፍ ድርብ
ይሁን። [16] ሰዎችን ከእግዚአብሔር የሚያ
ርቅ መጥፎ ክርክር ይቅርብህ። [17] እንዲህ
ያለው ክርክር ሰውን ያቆስላል ፥ ያቃጥላ
ልም። ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ እንዲህ ያለውን
ጎጂ ክርክር ከሚወዱት ሰዎች መካከል
ናቸው። [18] በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ሰዎች

ጭልጥ ብለው ከስሕተት ውስጥ ወድቀ
ዋል። እንዲያውም ፣ «የሙታን ትንሣኤ
ከዚህ በፊት ሆኖአል» እያሉ በማስተማር
የአንዳንዶችን ሰዎች እምነት አናውጠዋል።
19 ይሁን እንጂ ፣ እግዚአብሔር የመሠረ
ተው ጠንካራ መሠረት በፍጹም ሊናወጥ
አይችልም። ምክንያቱም ፣ «ጌታ የእርሱ
የሆኑትን ያውቃል» እንዲሁም ፣ «ፈሪሃ
እግዚአብሔር አለኝ የሚል ሁሉ ከዓመፅ
ይራቅ» የሚሉ ቃሎች በዚህ መሠረት ላይ
ተጽፈዋል።
20 በአንድ ሀብታም ቤት ውስጥ ከወር
ቅና ከብር እንዲሁም ከእንጨትና ከሸክላ
የተሠሩ ዕቃዎች ይገኛሉ። በጣም ውድ
የሆኑት ዕቃዎች የክብር እንግዳ ሲመጣ
ይቀርባሉ። መናኛ የሆኑት ዕቃዎች ግን
በማዕድ ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ ፣ ወይም
የትራፊ ማጠራቀሚያ ይሆናሉ። 21 አንተም
ከኃጢአት ርቀህ ብትቀደስ፣ ልክ እንደተከበ
ሩት ዕቃዎች ጌታ ክፍ ባለ ሥራ ላይ ያው
ልሃል።
22 ከወጣትነት ክፉ ምኞት ራቅ። ጽድ
ቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን አጥብቀህ
ያዝ። በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚያመልኩ
ሰዎች ጋር ሕብረት ይኑርህ። 23 ላስጠነቅ
ቅህ የምፈልገው ነገር ቢኖር፣ ጠብን ከሚቀ
ሰቅስ የሞኝነት ክርክር እንድትርቅ ነው።
24 ምክንያቱም የክርስቶስ አገልጋይ የሆነ
ሰው ትዕግሥተኛና ጨዋ ፣ የተሳሳቱትንም
የሚያርም መሆን ይገባዋል እንጂ የጠብያ
ለህ ማለት አይገባውም። 25 እውነቱን የሳቱ
ሰዎች ንስሓ ገብተው ወደ እግዚአብሔር
ሊመለሱ ስለሚችሉ ከስሕተታቸው እንዲታ
ረሙ በርኅራኄና በትሕትና እርዳቸው።
26 እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ሰይጣን ፈቃ
ዱን እንዲፈጽሙ እጅ እግራቸውን አሥሮ
የኃጢአት ባሪያ አድርጓቸዋል። ሆኖም ስሕ
ተታቸውን በመገንዘብ ከሰይጣን እጅ አም
ልጠው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈ
ጸም፣ የንስሐ ዕድል አላቸው።

## ምዕራፍ 3

1 ጢሞቴዎስ ሆይ ፣ በመጨረሻው ዘመን
ክርስቲያን ሆኖ መገኘት በጣም እንደሚያስ
ቸግር እወቅ። 2 ምክንያቱም ሰዎች ራሳቸ
ውን የሚወዱና ለገንዘብ የሚስገበገቡ ፣ ትዕ
ቢተኞችና ጉረኞች ፣ ተሳዳቢዎችና ለወላጆ
ቻቸው የማይታዘዙ ፣ የማያመሰግኑና ቅድስና
የሌላቸው ፣ 3 ልበ ደንዳኖችና ውሸተኞች ፣
ሁከተኞችና ጨካኞች ፣ ንጽሕና የጐደላቸ
ውና መልካም ኑሮ ለመኖር በሚፈልጉት
ላይ የሚያፌዙ ቀልደኞች ይሆናሉ። 4 እን
ዲሁም ባልንጀሮቻቸውን የሚክዱና ችኩ
ሎች ፣ በትዕቢት የተወጠሩና እግዚአብሔርን
ከማምለክ ይልቅ የዚህን ዓለም ደስታ የሚ
ወዱ ይሆናሉ። 5 ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄ
ዳሉ ፣ የአምልኮን ሥርዓት አያጓድሉም፤ ነገር
ግን የሚሰሙትን እውነት በተግባር አያው
ሉትም። እነዚህን ከመሳሰሉ ሰዎች ራቅ።
6 የኃጢአት ቀንበር ወደ ተጫናቸውና
ለልዩ ልዩ ክፉ ምኞት ወደሚገዙ ፣
ሞኞች ሴቶች ቤት በሹልክታ እየገቡ ፣
አዲስ ትምህርታቸውን የሚያስተምሩ እን
ደነዚህ ያሉት ሰዎች ናቸው። 7 እንዲህ
ዓይነቶቹ ሴቶች ሁልጊዜ እውነትን እየተ
ማሩ ነገር ግን ማወቅና መረዳት ስለማይ
ችሉ አዳዲስ ትምህርትን በቀላሉ ይከተ
ላሉ። 8 ኢያኔስና ኢያንበሬስ ሙሴን እንደ
ተቃወሙት ሁሉ እነዚህም ሰዎች ጠማ
ማና ክፉ አሳብ ስላላቸው እውነትን ይቃ
ወማሉ። ከክርስትና እምነትም የራቁ ከሃ
ዲያን ናቸው።
9 ኢያኔስና ኢያንበሬስ ስሕተተኞች
መሆናቸው ይፋ እንደወጣ ሁሉ ፣ የእነዚ
ህም ሰዎች ስሕተት አንድ ቀን ይገለጣል።
10 አንተ ግን ትምህርቴን፣ ጠባዬን፣ ዓላማ
ዬን ፣ እምነቴን፣ ትዕግሥቴን፣ ፍቅሬንና ጽና
ቴን አንድ በአንድ ታውቀዋለህ። 11 ወንጌ
ልን በመስበኬ የደረሰብኝን ስደትና መከራ
ሁሉ ታውቃለህ። በአንጾኪያና በኢቆንዮን፣
በልስጥራም ምን እንዳጋጠመኝና ከደረሰብ
ኝም ሁሉ ጌታ እንደ አዳነኝ ከአንተ የተሰ
ወረ አይደለም። 12 እግዚአብሔርን መስለው
ለመኖርና ክርስቶስን ለማስደሰት የሚፈልጉ
ሁሉ ይሰደዳሉ። 13 ክፉ ሰዎችና ሐሰተኞች
አስተማሪዎች ግን ራሳቸው በሰይጣን ተታ
ለው ፣ ሌሎችን እያሳሳቱና በክፋት ላይ
ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ።
14 አንተ ግን በተማርከው ትምህርት ጸን
ተህ ቁም። ምክንያቱም ይህንን እውነት
ከማን እንደተማርከው ታውቃለህ። 15 ገና
ከሕፃንነትህ ጀምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን
ተምረሃል። በክርስቶስ ኢየሱስ በእምነት
ስለሚገኘው ደኅንነት ለመረዳት የቻልከ
ውም በእነርሱ አማካይነት ነው። 16 መጽ
ሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ መሪ
ነትና ቀስቃሽነት ነው። ቃሉም እውነትን
ያስተምረናል። የተሳሳትንበትንም ስሕተት
በማሳየት ከስሕተታችን እንድንታረምና በቅ
ድስና እንድንኖር ይረዳናል። 17 እንደ እግዚ

አብሔር አገልጋዮችም ፣ ለመልካም ሥራ
ሁሉ እንድንዘጋጅ ያስችለናል።

## ምዕራፍ 4

[1] በእግዚአብሔር ፣ እንደዚሁም በክብሩና
በኃይሉ ተገልጦ በሕያዋንና በሙታን ላይ
በሚፈርደው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት ፣ ይህ
ንን አደራ እልሃለሁ። [2] ምን ጊዜም ቢሆን፣
ቢመችህም ባይመችህም ቃሉን ስበክ ፣ ገሥ
ጽም። ሰዎች ትክክል የሆነውን ነገር እንዲ
ያደርጉ እያደፋፈርክ በትዕግሥት የእግዚአ
ብሔርን ቃል መግባቸው።
[3] ምክንያቱም ሰዎች ፣ እውነተኛውን
ትምህርት ሳይሆን ለሥጋዊ አእምሮአቸው
የሚስማማውን ፍልስፍና ብቻ የሚያስተም
ሩትን አስተማሪዎች ፍለጋ ወዲያና ወዲህ
የሚሯሯጡበት ዘመን ይመጣል። [4] መጽ
ሐፍ ቅዱስ የሚለውን እውነት በመስማት
ፈንታ የራሳቸውን የተሳሳተ ፍልስፍና ይከ
ተላሉ። [5] አንተ ግን ጸንተህ ቁም። ለጌታም
ስትል መከራ ለመቀበል ተዘጋጅ። ለወንጌል
መስፋፋት የምትሰጠውን አገልግሎት ሳታ
ቋርጥ በትጋት ወደፊት ግፋበት።
[6] ይህንን ሁሉ እንድነግርህ የተገደድኩ
በት ዋና ምክንያት ከእንግዲህ ወዲህ በአጠ
ገብህ ተገኝቼ ብዙ ልረዳህ ስለማልችል
ነው። ሕይወቴ የሚሠዋበትና ከዚህ ዓለም
የምለይበት ጊዜ ተቃርቧል። [7] እስከ አሁን
ድረስ መልካሙን ውጊያ ተዋግቻለሁ።
ሩጫዬን ፈጽሜአለሁ። በእምነቴም ጸንቼ
ቆሜአለሁ። [8] ከዚህ በኋላም ጻድቅ ፈራጅ
የሆነው ጌታ በዚያች ቀን የሚሸልመኝ የጽ
ድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል።
ይህም የጽድቅ አክሊል የሚሰጠው ለእኔ
ብቻ ሳይሆን የእርሱን መምጣት በተስፋ
ለሚጠባበቁ ሁሉ ነው።
[9] የሚቻልህ ከሆነ ወደ እኔ በቶሎ ና።
[10] ዴማስ የዚህችን ዓለም ነገር ወድዶ እኔን
ትቶ ወደ ተሰሎንቄ ሄዷል። ቄርቂስ ወደ
ገላትያ ፣ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ለአገልግ
ሎት ሄደዋል። [11] አሁን ከእኔ ጋር ያለው
ሉቃስ ብቻ ነው። ማርቆስ በአገልግሎቴ
ስለሚረዳኝ ይዘኸው ና። [12] ቲኪቆስን ወደ
ኤፌሶን ልኬዋለሁ። [13] ስትመጣ በጢሮአዳ
ከወንድም አክርጳ ዘንድ የተውኳቸውን
ካፓርትና መጻሕፍት ፣ በተለይም በብራና
የተጻፉትን መጻሕፍት ይዘህልኝ ና።
[14] ናስ አንጣሪው እስክንድሮስ የሠራኝ
ክፉ ነገር እንዲህ እንዳይመስልህ ፣ በጣም
ነው የጐዳኝ። ጌታ ዋጋውን ይከፍለዋል!
[15] እኛ የምናስተምረውን ሁሉ የሚቃወም
ሰው መሆኑን አውቀህ ከእርሱ መጠንቀቅ
ይኖርብሃል።
[16] በመጀመሪያው ቀጠሮ ፍርድ ቤት
ስቀርብ ማንም ደጋፊ አልነበረኝም።
ሁሉም ሰው ተለየኝ። ሆኖም ይህን አድራጎ
ታቸውን እግዚአብሔር አይቁጠርባቸው።
[17] ጌታ ግን ከጎኔ ቆሞ አበረታትቶኛል።
በፍርድ ቤት ውስጥ ተሰብስቦ ለነበረው የአ
ሕዛብ ወገንም ፣ የወንጌልን መልእክት ሙሉ
ለሙሉ እንዳበሥር ኃይል ሰጥቶኛል። 'ከአ
ንበሳም አፍ' አድኖኛል። [18] አዎን ፣ ጌታ
ሁልጊዜ ከክፉ ሁሉ ይጠብቀኛል። ወደ
ሰማያዊ መንግሥቱም ያስገባኛል። ለእርሱ
ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፣
አሜን።
[19] እባክህን ለአቂላና ለጵርስቅላ እንዲ
ሁም ለሄኔሲፎሩም ቤተ ሰቦች የከበረ ሰላም
ታዬን አቅርብልኝ። [20] ኤርስጦስ ያለው ቆሮ
ንቶስ ከተማ ነው። ጥሮፊሞስ ደግሞ ስለ
ታመመ በሚሊጢን ትቼዋለሁ።
[21] ክረምት ከመግባቱ በፊት ከእኔ ዘንድ
ለመድረስ ሞክር። ኤውግሎስ ፣ ጱዴስ ፣
ሊኖስ ፣ ቅላውዲያና ከዚህ ያሉት ክርስቲያ
ኖች በሙሉ የከበረ ሰላምታቸውን ያቀርቡ
ልሃል። [22] ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስህ
ጋር ይሁን። ጸጋም ይብዛልህ።

መንፈሳዊ አባትህ
ጳውሎስ

# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለቲቶ የጻፈው መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፣የተጻፈበት ጊዜ ደግሞ በ63 ዓ.ም. አካባቢ ነው። ይህ መልእክት ለጢሞቴዎስ ከተላኩት ሁለት መልእክቶች ጋር ተመሳሳይነት አለው። አንድ የክርስቶስ አገልጋይ የሆነ ደቀመዝሙር፣በሥነ ምግባሩ እጅግ የተመሰገነና በትምህርቱም ሆነ በኑሮው ጠንቃቃ መሆን እንዳለበት ያሳስባል። መልእክቱ፣በእግዚአብሔር ጸጋ ከኃጢአት ባርነት ነፃ የሆነ ማናቸውም ሰው በአኗኗሩ ይህንኑ ዓለማ መከተል እንዳለበት ያስገነዝባል።

---

## ምዕራፍ 1

1-2 የእግዚአብሔር አገልጋይና የኢየሱስ
ክርስቶስ መልእክተኛ ከሆነው ከጳውሎስ
የተላከ። በእግዚአብሔር የተመረጡ ሁሉ
እምነት እንዲቀዳጁና ወደ እውነተኛው
ሃይማኖት የሚያደርሰው እውነት ምን እን
ደሆነ እንዲያውቁ ለማስተማር ተልኬአ
ለሁ። ይህም የማስተምረው እውነት የሰውን
ሕይወት የሚለውጥ፣ ሐሰትን የማይናገረው
እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ለሚያምኑት
ሁሉ ሊሰጥ ቃል የገባውን የዘላለም ሕይ
ወት ተስፋ የሚያበሥር ነው። 3 ትክክለ
ኛው ዘመን በደረሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር
ይህን የዘላለምን ሕይወት ተስፋ፣በተሰበከው
የወንጌል ቃል አማካይነት ይፋ አውጥቶ
ታል። ይህንንም የምሥራች ቃል በአዳኛ
ችን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለሰዎች ሁሉ
እንዳውጅ አደራ ተቀብያለሁ።
4 በጌታ ላይ ባለን የጋራ እምነት እውነ
ተኛ ልጄ ቲቶ ሆይ፣ከእግዚአብሔር አባታ
ችን፣ከአዳኛችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገ
ኘው ሰላምና በረከት እንዲበዛልህ እመኝል
ሃለሁ።
5 በቀርጤስ ትቼህ የመጣሁት፣ በዚያ
የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በሚጎድላ
ቸው ነገር ሁሉ በሥርዓት እንዲደራጁ በበ
ኩልህ ጥረት እንድታደርግና በሰጠሁህም
መመሪያ መሠረት፣ ምዕመናኑን ለማገልገል
የሚችሉትን ሽማግሌዎች በየከተማው እን
ድትሾም ነው። 6 እነዚህም የሚሾሙት
የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አንድ
ሚስት ብቻ ያላቸው፣ ልጆቻቸው ጌታን
የሚወዱና በአካባቢያቸው በሚገኙት
ሰዎች ዘንድ በባለጌነትና ወላጆቻቸውን ባለ
መታዘዛቸው ምክንያት ስማቸው በመጥፎ
የማይነሣ መሆን አለበት።
7 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የእግዚ
አብሔር አገልጋዮች ስለሆኑ በማንም ሰው
የሚነቀፍ ሕይወት የማይኖሩ፣የማይኮሩ፣
የማይቆጡ፣የማይሰክሩ፣ጨካኞች ያልሆኑና
ለገንዘብ የማይስገበገቡ መሆን አለባቸው።
8 በአንጻሩ ግን እንግዳ ተቀብለው የሚያስተ
ናግዱ፣ በጎ የሆነውን ነገር ሁሉ የሚወዱ፣
ራሳቸውን መቆጣጠር የሚችሉ፣ ሐቀኞች፣
የተቀደሱና ጨዋዎች መሆን ይገባቸዋል።
9 በተለይም የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ
በማወቅና የተሰጣቸውን መንፈሳዊ ቅርስ
አጥብቀው በመያዝ፣አማኞች በእምነታቸው
እንዲጸኑ የሚያስተምሩና ከቃሉም ርቀው
የተሳሳተ መንገድ የሚከተሉትን በማረም፣
እውነቱን ማስረዳት የሚችሉ መሆን አለባ
ቸው።
10 ይህንንም ለመናገር የቻልኩበት ምክን
ያት፣ «ክርስቲያን ግዝረትንና ሌሎችንም
የአይሁድ ሕግ መታዘዝ አለበት» እያሉ
የሚሟገቱና መታረምም፣የሚያስፈልጋቸው
ብዙ ሰዎች በመካከላችሁ እንዳሉ ስለማ
ውቅ ነው። የእነርሱ አስተሳሰብ ምኞት
ከመሆን አልፎ ሰዎች እውነትን መመልከት
እንዳይችሉ ያደናግራል። 11 ስለዚህ እንዲህ
ያለው ነገር በአጭር መቀጨት አለበት።
እስከ ዛሬ ድረስ እንኳ በእነዚህ ሰዎች አነ
ጋገር በመታለል ስንት ቤተሰቦች ከእግዚአ
ብሔር ጸጋ ተለይተው እንደቀሩ ታውቃላ
ችሁ። የእነዚህ ሐሰተኞች አስተማሪዎች
ፍላጎት ገንዘባችሁን ለመበዝበዝ መሆኑን
እንድታውቁ ይገባል። 12 የራሳቸው ሰው

የሆነው አንድ የቀርጤስ ነቢይ እንኳ ስለ
እነርሱ ሲናገር፥ «የቀርጤስ ሰዎች ውሸታ
ሞች፥አደገኞች እንስሶችና ለሆዳቸው ብቻ
ያደሩ ሰነፎች ናቸው» ብሏል። 13 በእር
ግጥ ይህ ሰው እውነት ተናግሯል! ስለዚህ
አንተም ራስህ ብትሆን ክርስቲያኖች በእ
ምነታቸው መሠረት ላይ ጸንተው እንዲ
ቆሙ፥ምንም ሳታመነታ የማስተማርና የማ
ረም ግዴታ አለብህ። 14 በተለይም በአይሁ
ዶች ተረትና ከንቱ አሳብ እንዳይታለሉና
እንዳይመረዙ በሚገባ ማስጠንቀቅ ይኖርብ
ሃል።
15 ልባቸው ንጹሕ የሆነ ሰዎች ለማንኛ
ውም ነገር መልካምና ንጹሕ አመለካከት
አላቸው። ነገር ግን የማያምኑና በክፋት
የተሞሉ ሰዎች፥ የሚያጋጥማቸውን ነገር
ሁሉ የሚመለከቱት በክፋት ዓይን ነው።
ምክንያቱም አእምሮአቸውና ሕሊናቸው
ረክሷልና። 16 በጣም የሚያስገርመው፥ እነ
ዚህ ሰዎች፥ «እግዚአብሔርን እናውቃለን»
እያሉ መናገራቸው ነው። ኑሮአቸውንና
ሥራቸውን ለሚታዘብ ግን፥ «እግዚአብሔ
ርን እናውቃለን» ብለው የሚናገሩት በአፍ
ብቻ እንጂ በተግባር እንደሚክዱት ማስተ
ዋል አያቅትም። በተጨማሪም እነዚህ
ሰዎች ርኩሶችና አመፀኞች፥እንዲሁም ለም
ንም የማይጠቅሙ መሆናቸውን በቀላሉ
መረዳት አያዳግትም።

## ምዕራፍ 2

1 አንተ ግን ትክክለኛ የሆነ የክርስትና
እምነት ምን እንደሆነ አስተምር። 2 በዕ
ድሜ ጠና ያሉትን ወንዶች የተረጋጉ እንዲ
ሆኑና በመጠን እንዲኖሩ፥እንዲሁም ደግሞ
እምነትን፥ፍቅርን፥በእውነት ጸንቶ መቆምን
እንዲያውቁ አስተምራቸው።
3 አሮጊቶችም በነገር ሁሉ ረጋ እንዲ
ሉና ክብራቸውን እንዲጠብቁ አሳስባቸው።
በተለይም መልካም ነገርን ከማስተማር
ፈንታ መንደር ለመንደር እየዞሩ ሐሜተኞ
ችና ጠጪዎች ሆነው ከመገኘት እንዲቆ
ጠቡ በሚገባ ምከራቸው። 4 እነዚህም አሮ
ጊት እናቶች፥ወጣት ሴቶችን ጨዋ የትዳር
እመቤቶች እንዲሆኑ፥ለባሎቻቸውና ለልጆ
ቻቸውም ፍቅር እንዲኖራቸው፥ 5 ጠንቃቆ
ችና ንጹሓን እንዲሆኑ፥ጊዜያቸውን ለቤተሰ
ባቸው እንክብካቤ እንዲያውሉ፥ ቸሮችና
ለባሎቻቸው ታዛዦች እንዲሆኑ ያስተምሯ
ቸው። በዚህ መልካም ሕይወት ቢመላለሱ
የእግዚአብሔር ቃል ይከበራል፤ ሰዎችም
አኗኗራችንን የሚነቅፉበት ምክንያት አይኖ
ራቸውም።
6 እንዲሁም ደግሞ ጎልማሶች በጣም
ጥንቁቆች ሆነው ራሳቸውን በመቆጣጠር
እንዲኖሩ ምከራቸው። 7 በተለይም አንተ
በምትናገረውና በምታደርገው ነገር ሁሉ፥
እውነተኛነትህንና ቁም ነገረኛነትህን እንዲ
ያዩ በማድረግ ጥሩ ምሳሌ ሁናቸው። 8 ስታ
ስተምርም፥ የሚቃወሙህ ሰዎች ለነቀፋ
የሚሆን ምክንያት እንዳያገኙብህ ከአንደበ
ትህ የሚወጣው ቃል ሁሉ ቁም ነገር የተ
ሞላበት ይሁን።
9 አገልጋዮች አስተዳዳሪዎቻቸውን በሁ
ሉም አቅጣጫ እንዲታዘዙና እንዲያስደስቱ
አቸው፥ ክፉ ቃልም እንዳይመልሱላቸው፥
10 ይልቁንም ታማኝ ሆነው እንዲገኙ እንጂ
እንዳይሰርቁ ምከራቸው። ምክንያቱም የእነ
ርሱን ጨዋነትና ታማኝነት የተሞላበት ኑሮ
በማየት፥ ሌሎች ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ
እንዲያምኑ ፍላጎት ያድርባቸዋል።
11 እግዚአብሔር የዘላለም ደኅንነት
ጸጋን ለሰዎች ሁሉ ልኮአል። 12 ይህንንም
ጸጋ የተቀበለ፥ከዓለማዊ ምኞትና በኃጢአት
ከመኖር ተለይቶ በዚህ ዓለም ራስን በመግ
ዛት፥ እግዚአብሔርን በመፍራትና በጽድቅ
እንዲኖር ተጠርቶአል። 13 ይህም ጸጋ የታ
ላቁ አምላካችንና የአዳኛችን የኢየሱስ ክር
ስቶስ ክብር የሚገለጥበትን ቀን በተስፋ እን
ድንጠባበቅ ያደርገናል። 14 ክርስቶስም ከኃ
ጢአት ሊያድነንና ሊያነጻን ወገኖቹም
ሆነን በጎ ተግባር ለመፈጸም ፍላጎት ሊያሳ
ድርብን፥የእግዚአብሔርን የኃጢአት ፍርድ
በመቀበል ለእኛ ሲል ሞቶልናል።
15 ስለዚህ ይህን ነገር አጥብቀው እንዲከ
ተሉ ምዕመናኑን በጥሞና አስተምራቸው።
የሚሳሳቱትንም በምክርና በተግሣጽ መልሳ
ቸው። ማንም ቃልህን አቃልሎ እንዲመለከ
ተው አትፍቀድለት።

## ምዕራፍ 3

1 ለመንግሥትና ለባለሥልጣን ሁሉ እን
ዲታዘዙና በመልካም ተግባር ሁሉ እንዲሳ
ተፉ፥ 2 ለማንም ክፉ በመመለስና በመጣ
ላት ፈንታ በሰላም መኖርን እንዲያውቁና
ለሰው ሁሉ ከልብ የሆነ ትሕትና እንዲያ
ሳዩ አስተምራቸው።
3 እኛም ብንሆን አንድ ጊዜ የክፉ
ምኞት ተገዢዎችና መታዘዝን የማንወድ፥
በቀላሉ የምንታለልና ወደ ርኩስ ፍላጎት
የምንሳብ፥በመጥፎ ልማዶችም የታሠርንና፥

ቅናት ፥ ጥላቻ ፥ ተንኰልና የእርስ በእርስ ጠብ የሞላብን ነበርን።
[4]ነገር ግን አዳኛችን እግዚአብሔር በጎነቱንና ፍቅሩን በገለጠልን ጊዜ ደህንነትን አገኘን። [5]ይህንን መዳን ያገኘነው ብቁ ሆነን በመገኘታችን ሳይሆን ፥ ከምሕረቱ ብዛት የተነሣ ነው። ስለዚህ ከኃጢአታችን አንጽቶ በመንፈስ ቅዱስ በማደስ ለአዲስ ልደት አብቅቶናል። [6]ይህንንም መንፈስ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በሙላት በሕይወታችን ውስጥ አፈሰሰው። [7]ይህንንም ያደረገው በጸጋው ጸድቀን በተስፋ የምንጠባበቀውን የዘላለም ሕይወት ወራሾች እንድንሆን ነው። [8]የነገርኩህ ሁሉ እውነተኛ ነገር ስለሆነ ክርስቲያኖች ምክርህን ተቀብለው መልካም ማድረግን እንዲማሩ ፥ በጥብቅ አሳስባቸው። እነዚህ ነገሮች ለሰው ሁሉ እጅግ መልካምና ጠቃሚም ናቸው።
[9]ነገር ግን ምንም ፍሬ ከሌለው ከንቱ ከሆነ ክርክርና ጭቅጭቅ እንድትቆጠብ ላሳስብህ እወዳለሁ። በተለይም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ከሚያመዝነው «የአይሁድን ሕግ መጠበቅ ይገባል? ወይስ አይገባም?» ከሚለው ከንቱ ክርክር ራቅ። [10]በተሳሳተ ትምህርቱ ልዩነትን የሚፈጥር ሰው ካለ፥የመለያየት ተግባሩን እንዲያቆም አንድ ወይም ሁለት ጊዜ አስጠንቅቀው። በዚህ ዓይነት መክረኸው እምቢ የሚል ከሆነ ግን፥እንዲህ ካለው ሰው ራቅ። [11]ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሰው አስተሳሰቡ የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን ፥ ኃጢአት የሚያደርገውም ሆነ ብሎ ነውና በራሱ ላይ ፈርዶአል።
[12]አርጢሞንን ወይንም ቲኪቆስን ወደ አንተ እልካለሁ። ይህንን ክረምት አሳልፋለሁ ብዬ ያሰብኩት በኒቆጵልዮን ስለሆነ ከሁለት አንዳቸው እንደመጡ ወደዚያው ብቅ በልና እንገናኝ። [13]ዜማስ የተባለውን የሕግ አዋቂና አጵሎስን ለጉዞ በሚያስፈልጋቸው ሁሉ የሚቻልህን ያህል እርዳታ አድርገህላቸው በቶሎ ሸኛቸው። [14]የኛ ሰዎች በበጎ ሥራ እየተጉ እርዳታ የሚያስፈልገውን ሰው መርዳትንና ፍሬያማ ተግባር መፈጸምን ይማሩ።
[15]አብረውኝ ያሉት ሁሉ ሰላምታቸውን ያቀርቡልሃል። አንተም አብረውህ ላሉት ክርስቲያን ወዳጆቻችን ሁሉ የከበረ ሰላምታችንን አቅርብልን።
የእግዚአብሔር ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

ያንተው
ጳውሎስ

# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለፊልሞና የጻፈው መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበትም ጊዜ በ62 ዓ.ም. መሆኑ ይገመታል። ከፊልሞና አገልጋዮች አንዱ አናሲሞስ የተባለው፥ከድቶ ከቆላስይስ ወደ ሮም ይኮበልላል። ሐዋርያው ጳውሎስም በሮም አግኝቶ ከመሰከረለት በኋላ አናሲሞስ በክርስቶስ ያምናል። ሐዋርያውም፥ወዳጁ ፊልሞና አናሲሞስን እንዲታረቀውና እንደ ክርስቲያን ወንድሙ አድርጎ እንዲቀበለው፥ይህን መልእክት አስይዞ ይልከዋል።

---

[1-2]የክርስቶስን ወንጌል በማስተማሩ ምክንያት በወህኒ ቤት ታሥሮ ከሚገኘው ከጳውሎስና ከወንድም ጢሞቴዎስ የተላከ። እጅግ ለምንናፍቅህና ለምናፈቅርህ ለሥራ ባልደረባችን ለፊልሞና ፥ ለእህታችን አፍብያና እንደ እኛ የክርስቶስ ወታደር ለሆነው አርክጳ፥እንዲሁም በቤትህ ውስጥ ለጸሎትና ለአምልኮ ለሚሰበሰቡት ምዕመናን በሙሉ።
[3]የአባታችን የእግዚአብሔር፥የጌታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም እንዲበዛላችሁ እየተመኘን ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን።

4 የተወደድከ ወንድሜ ፊልሞና ሆይ ፥
ስለ አንተ በምጸልይበት ጊዜ ሁሉ እግዚአ
ብሔር አምላኬን አዘውትሬ አመሰግናለሁ።
5 ለዚህም ምክንያት የሚሆነኝ ፥ በየጊዜው
የምሰማው በጌታ ኢየሱስ ላይ ያለህ ጠንካራ
እምነት ፥ እንዲሁም ለእርሱና ለክርስቲያን
ወገኖች የምታሳየው ፍቅር ነው። 6 አሁንም
ቢሆን ስለ እምነትህ ለሰዎች በምትመሰክር
በት ጊዜ ልባቸው እንዲነካና በአንተ ሕይ
ወት ምሳሌነት የበረከት ሁሉ ምንጭ ክርስ
ቶስ መሆኑን እንዲረዱ እጸልይልሃለሁ።
7 ወንድሜ ፊልሞና ሆይ፥በየጊዜው በምታሳ
ያቸው ፍቅር ምክንያት ፥ የክርስቲያኖች
ልብ ስለተነካና ስለረካ እኔም ታላቅ ደስ
ታና መጽናናት አግኝቼአለሁ።

8-9 አንድ ነገር ልለምንህ እወዳለሁ።
እንደ እውነቱ ከሆነ በክርስቶስ ወንድማ
ማች ስለሆንን ይህን የምለምንህን ጉዳይ
አድርግልኝ ብዬ በቀጥታ ላዝህም እችል
ነበር። ነገር ግን ከማዝህ ይልቅ የምጠይቅ
ህን እንድትፈጽምልኝ በፍቅር ልለምንህ
መርጫለሁ። እንደምታውቀው ፥ «ለምን
ጌታን አገለገልክ» ተብዬ ይኸው በስተእር
ጅናዬ በእሥር ላይ እገኛለሁ።

10 እንድትፈጽምልኝ የምለምንህ ጉዳይ፥
በእሥር ላይ ሆኜ ወንጌልን ሳስተምር
ሰምቶ ፥ በክርስቶስ በማመን የመንፈስ ልጄ
የሆነውን አገልጋይህን አናሲሞስን ፥ በይቅ
ርታ እንድትቀበለው ነው። 11 ከዚህ በፊት
አናሲሞስ ለአንተ የሚረባ ምንም ነገር እን
ዳላደረገ አውቃለሁ። አሁን ግን እንዲህ
አይምሰልህ! ለአንተም ሆነ ለእኔ በጣም
የሚጠቅም ሰው ወጥቶታል። 12 እርሱንም
ወደ አንተ እንዲመለስ ልኬዋለሁ። እርሱን
ስልክ የእኔም ልብ አብሮት እንደመጣ
ያህል ቁጠረው።

13 «ወንጌልን ለምን ትሰብካለህ» ተብዬ
በሰንሰለት ታሥሬ ባለሁበት በአሁኑ ጊዜ
አናሲሞስ እንደ አንተው ሆኖ ብዙ ሊረዳኝ
ይችል ነበር። 14 ይሁን እንጂ አንተን ሳላስ
ፈቅድ እሱን ከእኔ ጋር ማስቀረቱ ትክክል
መስሎ አልታየኝም። ምክንያቱም የምታደ
ርግልኝ ማንኛውም በጎነት በልብ ፈቃደኝ
ነት እንጂ ተገፋፍተህ መሆን ስለሌለበት
ነው። 15 ምናልባት አናሲሞስ ከቤትህ ለጥ
ቂት ጊዜ ሸሽቶ መሄዱም፥አሁን በክርስቶስ
ካገኘው የሕይወት ለውጥ የተነሣ ፥ወዳንተ
ሲመለስ ዳግም ላይለይህ ፥ ወዳጅነታችሁ
ከፊት ይልቅ የጸና እንዲሆን ይሆናል።
16 ደግሞም ከአሁን በኋላ እንደ ድሮው አገ
ልጋይህ ብቻ አይደለም ፥ ከአገልጋይም የበ
ለጠ በክርስቶስ ወንድምህ ስለሆነ እኔ የም
ወደውን ያህል አንተም ከልብ እንደምትወ
ደው አልጠራጠርም።

17 በእርግጥ እኔን እንደ ወዳጅህ አድር
ገህ የምትቆጥረኝ ከሆነ እሱንም እንደ እኔ
አድርገህ ተቀበለው። 18 ከዚህ በፊት በድሎ
ህም ወይም ሰርቆህም ቢሆን ዕዳውን ሁሉ
በእኔ ላይ አድርገው። 19 እሱ ያለበትን ዕዳ
ሁሉ እኔ እንደምከፍልህ በዚህ በገዛ እጄ
በጻፍኩልህ ደብዳቤ ላረጋግጥልህ እወዳ
ለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ነፍስህ የዳነችው
በእኔ አገልግሎት ስለሆነ እርሱ ሊኖርበት
ከሚችለው ዕዳ የበለጠ፥የእኔ ውለታ አለብህ
ብዬ ማስታወሱ ተገቢ አይመስለኝም።
20 ስለዚህ የእኔ ወንድም ፥ እባክህን በጌታ
ስም የለመንኩህን እሺ በለኝና ከአሳብ
አርፌ እግዚአብሔርን ላመስግን።

21 ይህንን ደብዳቤ ስጽፍልህ የጠየቅኩ
ህን ይቅርና ከዚያም በላይ እንደምታደርግ
ልኝ ታዛዥነትህን በመተማመን ነው።

22 በተጨማሪም ፥ እግዚአብሔር የእናን
ተን ጸሎት ሰምቶ በቅርቡ ከእሥር ተፈትቼ
ወደ እናንተ እንድመጣ ያደርጋል ብዬ
ተስፋ ስለማደርግ የማርፍበትን ቦታ አዘጋጅ
ተህ ጠብቀኝ።

23 የክርስቶስን ወንጌል በማስተማሩ ምክ
ንያት ከእኔ ጋር ታሥሮ የሚገኘው ወንድማ
ችን ኤጳፍራ ሰላም ይልሃል። 24 እንዲሁም
የሥራ ባልደረቦቼ ማርቆስ ፥ አርስጥሮኮስ ፥
ዴማስና ሉቃስ ሰላምታቸውን ያቀርቡል
ሃል።

25 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመ
ንፈስህ ጋር ይሁን።

ወንድምህ
ጳውሎስ